## ምስጋናዬ ይድረሳቸው

1. መጀመሪያው "መጽሐፍ ቅዱስና ሙሐመድ" የተሰኘውን፣
2. "አዎ! ኢየሱስ ፈጣሪ ነው"
3. ይህን "ቁርዓን ስለ ክርስቶስ ምን ያውቃል?" የተሰኙትን እነዚህን ሦስት የመልስ መጻሕፍት ከመታተማቸው በፊት በግል አንብበውና በተለይ የመጀመሪያውን ጽሑፍ በሌሎች ሰዎች አስገምግመው በመልስ አሰጣጡም ሆነ በትምህርት ስጭነቱ አጥጋቢ ሆኖ ስላገኙት የማሳተሚያውን ገንዘብ በመለገስ ታትመው ለምንባብ እንዲበቁ ያደረጓቸው በጎ አድራጊ ምዕመን ኮሎኔል እምላዕሉ ወረደ ናቸው። እኚህ ውድ የቤተ ክርስቲያን ልጅ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በዘመኑ የነበሩት ፈታኞቹ ፈሪሳውያን "ለቄሳር ግብር መስጠት ይገባልን?" በማለት ላቀረቡለት ጥያቄ ገንዘቡን አይቶ "የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሔርን ለእግዚአብሔር ስጡ" ሲል የሰጣቸውን መልስና መመሪያ የተከተሉ ገንዘባቸውን ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን ግንባታ ያዋሉ (ገብር ኄር ወምዕመን) ታማኝ አገልጋይ ናቸው፤ ለእነዚህ ሕይወት አልባ ሆነው ለተወለዱ ድርሰቶቼ በቀይ ጥገና የሕይወት እስትንፋስ ሰጥተው ባፋቸው እንዲናገሩ የክርስቶስ አምላክነትና አዳኝነት ባደባባይ እንዲመሰክሩ ያደረጓቸው ሐኪም እምላዕሉ ወረደ ናቸው። ለኚህ የክርስትናው ኅብረተሰብ ታላቅ ባለውለታ ምዕመን የማቀርብላቸው ምስጋና ወደር ያለውም።

እንደዚሁም ይህን ድርሰት በኮምፒዩተር ቀርፆና አርሞ ያስረከበኝ ወጣት ሚካኤል ይባላል። ከሰጭው አሰጭው ነውና ይህን ወጣት ያስተባበሩልኝ አንድ የታወቁ በጎ አድራጊ ምዕመን ናቸው። ለነዚህ በጎ አድራጊ ወገኖቼ የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በረከቱን እንዲሰጣቸው በሰማይ የማያልፍ ርስቱን እንዲያወርሳቸው የዘወትር ምኞቴና ጸሎቴ ነው።



# መጽሐፍ ቅዱስና ሙሐመድ

### አይተዋወቁም

ከመምህር ኪዳነ ማርያም ጌታሁን

ለአህመድ ዲዳት የተሰጠ መልስ

www.ethiopianorthodox.org

# ምስጋና

ስማቸው ሊገለጥ ያልፈለጉ አንድ በጎ አድራጊ የማሳተሚያውን ዋጋ ከፍለው ስለአሳተሙልኝ ምስጋናዬ ወደር የለውም ፤

የብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ሠራተኞች በትሕትና ተቀብለውና ባጭር ጊዜ ውስጥ ሕትመቱን አቀላጥፈው ስለአስረከቡኝ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ፤

የእጅ ጽሑፉን በታይፕ ለመገልበጥ የረዱኝን ወ/ት ደስታ ጉልትነህንና ወ/ት ዓይኔአበባ ተረፈን ከልብ አመሰግናለሁ ፤ አምላክ ወልደ አምላክ የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ዋጋችሁን ይክፈላችሁ።

ለሰጠኝ ይስጥልኝ የረዳኝን ይርዳው ፤
የሰው ዓይን ያላየው እጅ ያልተጠበበው ፤
ሰማየዊ ዋጋ በላይ ቤት ይቆየው አሜን ።

ያለ ደራሲው ፈቃድ መልሶ ማሳተም ክልክል ነው

## ማውጫ

መግቢያ ........ 3
መጽሐፍ ቅዱስና ሙሐመድ ........ 5
እንደሙሴ ያለ ነቢይ ........ 7
ሦስት አለመመሳሰሎች ........ 11
የሙሴና የኢየሱ አጭር ታሪክ ........ 20
እስማኤል የበኩር ልጅ ........ 26
አስፈሪ ማስጠንቀቂያ ........ 29
ሦስት መጠይቆች ........ 31
ሁሉን መርምሩ ........ 33
የመጽሐፉ ባለቤቶች ........ 34
ይድረስ ለሙስሊሙ አፈቀላጤዎች ........ 37
የክርስቲያኖች መለኮታዊ መመሪያዎች ........ 38

www.ethiopianorthodox.org



**አዘጋጂው መምህር ኪዳነ ማርያም ጌታሁን**

**"በመንፈስህ ኃይል አጽናኝ ፤ ለሕገ ተላላፊዎች መንገድህን አስተምራቸው ዘንድ ፤ ኃጢአተኞችም ወደ አንተ ይመለሱ ዘንድ" መዝ·50 ቁ·12።**

## መቅድም

እግዚአብሔር የተወሰነ መኖሪያ ስፍራ የለውም ፡ በሰማይና በምድር ሙሉ ነው ፡ ስለልዕልናው በሰማይ አለ ይባላል ፡ የአምልኮቱ መጀመሪያ ቦታ ግን ይታወቃል ፡ የአምልኮቱ መጀመሪያ ቦታ እግዚአብሔርና አዳም የተነጋገሩባት ገነት ናት ፡

መመሪያው ሕገ ልቡና ነው ፡ እግዚአብሔር በሕገ ልቡና ተገልጦ ለአዳም የጸሎት ጊዜና ሰዓት ለይቶ አስተምሮታል ፡ ገነት የምትገኘው እግዚአብሔር ባወቀ ከሰማይ በታች ከምድር በላይ ተሰውራ ነው ፡ ሲአልም እንደዚሁ ናት ፡ ሰማይና ምድር ሲያልፉ ገነትና ሲኦልም አብረው ያልፋሉ ይጠፋሉ ፡ የነርሱን ቦታ መንግሥተ ሰማያትና ገሐነመ እሳት ይተካሉ (ይከፈታሉ) ፡ ራዕይ 21 ቁ 1 ተመልከት ፡

ሁለተኛ የብሉይ ኪዳን አምልኮት መነሻ ሙሴና እግዚአብሔር ቃል በቃል የተነጋገሩባት ደብረ ሲና ናት ፡ አምልኮቱ "አንድ አምላክን ማመን" ነው ፡ እግዚአብሔር አስሩን ትእዛዛት በጽላት ጽፎ ለሙሴ ሰጥቶታል ፡ ደብረ ሲና የምትገኘው በዓረብ ምድር በሲና በርሀ ውስጥ ነው ፡

ሶስተኛ በብሉይ ኪዳን ላይ የተመሠረተው የሐዲስ ኪዳን አምልኮት መነሻ መድኃኔ ዓለም ክርስቶስ የተወለደባት ፡ ያደገባት ፡ ወንጌልን ያስተማረባት ፡ የሞተባት፡ የተቀበረባት ፡ የተነሳባትና በኋላም ያረጋባት ኢየሩሳሌም ናት ፡ አምልኮቱ "ሥላሴ አንድም ሶስትም ናቸው" የሚል ነው ፡ ሶስት ስም አንድ እግዚአብሔር ማለት ነው ፡ ኢየሩሳሌም የምትገኘው በመካከለኛው ምሥራቅ በተስፋይቱ ምድር በከነዓን ውስጥ ስትሆን እነዳዊት እነሰሎሞን የነገሡባት ታሪካዊ ከተማ ናት ፡

አራተኛ የቁርዓን አምልኮት መነሻ መካ ናት ፡ መካ የምትገኘው በሳዋዲ ዓረቢያ ውስጥ ነው ፡ አምልኮቱ በከፊል /አንድ አምላክን/ በማመን ከብሉይ ኪዳን አምልኮት ጋር ይመስላል ፡ መሥራቹ ሙስሊሞች ነቢያችን የሚሉት ሙሐመድ ነው ፡

ሃይማኖቱ ከሐዲስ ኪዳን "ከክርስትና" አምልኮት ጋር ፈጽሞ አይቀራረብም ፡ እንዲያውም ለክርስትና ሃይማኖት ጠንቅ አስጣይ ነው ፡

www.ethiopianorthodox.org

የክርስትና ሃይማኖት ዶግማ "እግዚአብሔር ወልድ ወረደ ፡ ተወለደ ሞተ ተነሳ" የሚል ሲሆን የእስልምና ሃይማኖት ዶግሞ "አላህ አንድ ነው ፤ አይወልድም አይወለድም" የሚል ነው ፤ እንግዲህ በነዚህ ሁለት እምነቶች መካከል ያለውን ሰፊ ልዩነት እናንተው ልታመዛዝኑት ትችላላችሁ ፡ ማንም እንዲጠፋ የማይፈልገው ቸሩ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተለመደው አንድ ልዩ ተአምር ፈጥሮ በጎቹን ወደ አንድ በረት የሚሰበሰብበት ወቅት ሩቅ እንደማይሆን ተስፋ እናደርጋለን ፤ ምክንያቱም "እኔ ነኝ ቸር ጠባቂ ፤ በጎቼን አውቃለሁ ፡ በጎቼም ያውቁኛል ፤···· ስለበጎቼ ራሴን እለውጣለሁ ፤ ደግሞም ሌሎች በጎች አሉኝ ፡ ከዚህ መንጋ ያልሆኑ ፤ አመጣቸው ዘንድ ጊዜ አለኝ ፤ ቃሌን ይሰሙኛል ፤ እነርሱም ላንድ ጠባቂ አንድ መንጋ ይሆናሉ ብሏል፤ ዮሐ·10ቁ14–16

# መግቢያ

እግዚአብሔር ለስሙ መጥሪያ ለአምልኮቱ መታወቂያ እንዲሆኑ ከመረጣቸው አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ናት፣ ይኸውም ይታወቅ ዘንድ ቀደም ሲል እግዚአብሔር በነቢያት አድሮ ትንቢት አናግሮላታል፣ ነቢዩ ዳዊት ከክርስቶስ ልደት በፊት 2000 ዓመት ላይ "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች" ሲል ኢትዮጵያ ምንጊዜም እግዚአብሔርን የምታመልክ እግዚአብሔርም የሚወዳትና የአምልኮቱ መግለጫ እንድትሆን የመረጣት መሆኗን አስቀድሞ አረጋግጦላታል፣ ከዚህ የተነሳ ከእስራኤል ቀጥላ የሙሴን ሕግ ‹ኦሪትን› የተቀበለች ባንድ አምላክ ያመነች በኦሪቱ ህግና ሥርዓት 950 ዘመን ያህል እየተመራች የኖረች ሁለተኛ ሀገር ናት፣

5500 ዓመተ ፍዳ ዓመተ ኩነኔ ሲፈፀም ከሥላሴ አንዱ ወልድ ከቅድስት ድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው ሆኖ ‹ሥጋ ለብሶ› ወንጌልን አስተምሮ ለሰው ልጆች ደህንነት በምስቀል ላይ ሞቶ ከተነሳ በኋላ ኢትዮጵያ የተነገረው ትንቢት የተቆጠረው ሱባኤ እንደተፈፀመ አውቃ ሐዋርያ ሳይላክላት ኢየሩሳሌም ድረስ ሄዳ በክርስቶስ ስም ያመነች የተጠመቀች ቀዳሚት ሀገር ናት፤ የሐዋ.ሥራ 9ቁ.26፤ ከዚህ የተነሳ በአረቡ አለም የተከበበች ብቸኛ አፍሪካዊት የክርስትና ደሴት እየተባለች ትጠራለች።

ከ 600 ዓመተምሕረት በኃላ ሙስሊሞች ነቢያችን ነው የሚሉት ሙሐመድ በዓረቡ ዓለም ውስጥ ተነስቶ እስልምናን ሰበከ፣ ስብከቱም ለጊዜው ተቀባይ ባለማግኘቱ ከመካ ወደ መዲና ተሰድዶ ለአስር ዓመታት ያህል ኃይሉን ካጠናከረ በኋላ ወደ መካ ተመልሶ ተቃዋሚዎችን በማሸነፍ አዲሱን እምነት እንዲቀበሉት አድርጓል።

ሙሐመድ ለተከታዮቹ የሰጠው መመሪያ እንዳለ ይነገሬል፣ "እስላም በመሆናችሁ በሚደርስባችሁ ችግር ወደ ኢትዮጵያ ተሰደዱ፣ ክዚያ የሚነግሰው ንጉሥ እርሱ ሰው የማይበድል በርሱም ዘንድ ሰው የማይበደልበት ደግ ነው" የሚል ነው፤

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህ የተነሳ የሙሐመድ ቤተሰቦችና ጥቂት ተከታዬቹ ከተቃዎሚዎቻቸው በደረሰባቸው ተፅእኖ ወደ ኢትዬጵያ ተሰደው ጥገኞች ሆነዋል፣ ባላንጣዎቻቸው ተከታትለው እጃቸው እንዲሰጣቸው ቢጠይቁ ጥፋታቸው ምንድን ነው? ሰው ገድለዋልን? ወይስ ንብረት አጥፍተዋል? ሲል ንጉሡ ቢጠይቃቸው ሰው አልገደሉም፣ ንብረትም አላጠፉም፤ ሆኖም ስለምንፈልጋቸው እጃቸው ይስጠን አሉት፣ ንጉሡም ሰው ያልገደሉና ንብረት ያላጠፉ ከሆኑ ተላልፈው አይሰጡም በማለት ተቃዋሚዎችን ወደመጡበት መልሷቸዋል። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ሙስሊሞች በባብዕል መንደብ በኩል ወደ ኢትዬጵያ መጉረፍ ጀመሩ ይባላል።

የሙስሊሙ ኅብረተሰብ አብሮ ከመኖር የተነሳ የክርስቲያኑን ኅብረተሰብ ባህልና አኗኗር ሰላምና ትህትና እየተላበሰ መጣ፣ በእስላሞችና በክርስቲያኖች መካከል አበሮ የመኖሩ ውህደት እየጨመረ እንደመሄዱ መጠን የመከራውንም ሆነ የደስታውን የጦርነቱንም የነጻነቱን ጽዋ አብረው ሲቋደሱ ኖረዋል።

በኢትዬያ ውስጥ እስላሙና ክርስቲያኑ ኅብረተሰብ ከ 1400 ዘመን በላይ አብረው ሲኖሩ በመካከላቸው ሃይማኖታዊ ግጭት ተነስቶ አያውቅም፣ በቱርክ መንግስት አነሳሽነትና ድጋፍ ሰጭነት በምስራቅ ኢትዬጵያ በሀረርጌ ተነስቶ የነበረው ግራኝ መሀመድ ሰሜን ሸዋን ወሎን ትግራይንና ጎንደርን ለጊዜው ተቆጣጥሮ እንደነበረ ታሪክ ያስታውሰናል፣ ይኸውም በውጭ መንግስት ጣልቃ ገብነት እንጂ በኢትጵያውያን ሙስሊሞችና ክርስቲያኖች መካከል እንደተደረገ ግጭት የሚቆጠር አይደለም፣ ምክንያቱም ግራኝ መሀመድ በፖርቱጊዞች ርዳታ ከሞተ በኃላ ወዲያው ጦርነቱ ቆሟል፣ የእርስ ብርስ ግጭት ቢሆን ኖሮ ጦርነቱ ሊቀጥል በቻል ነበር።

አንዳንድ የአፍሪካ አምባገነን መሪዎች በሕዝባቸው መካከል በሚፈጥሩት አለመረጋጋት የእርስ በርስ ግጭቶች እየተነሱ ወደከፋ ጦርነት ሲሸጋገሩ በኢትዬጵያ ግን ነባር መሪዎች ወድቀው አዲሶቹ ስልጣን ቢያዙ ቁጥር እስላሙና ክርስቲያኑ ኅብረተሰብ ሰላሙንና አንድነቱን ከመጠበቅ በስተቀር የጎሳም ሆነ የሃይማኖት ግጭት አድርጎ አያውቅም፤ የሱማሌን የላይቤርያንና የሱዳንን የእርስ በርስ ግጭት ያየና የሰማው አለም ሁሉ የኢትዮጵያን ሕዝብ ጨዋነት እየተመለከተ ሲያደንቅ ይኖራል።

በዚህ ጨዋነታችንና ሰላማዊ ኑሯዋችን የቀኑብን ድንበር ዘለል አክራሪዎች የኢትዮጵያን ህዝብ በሃይማኖት ለመከፋፈል ክርስትናን የሚነቅፍ እስልምናን የሚደግፍ ሙጣጥፍ እያሳተሙ በአዲስ አበባ ከተማ ማሰራጨት ከጀመሩ ውለው አድረዋል፣ ይህ የአክራሪዎች ስውር አላማ ተቀባይ ይኖረዋል ብለን ባናምንም ለፅሁፋቸው ተገቢውን መልስ መስጠት አማራጭ የሌለው ጉዳይ ነው፣ ቁርዓንን የመተርጎምና የመተንተን መብት የሙስሊሙ ኅብረተሰብ ምሁራን የመሆኑን ያህል መጽሀፍ ቅዱስንም መተርጎምና መተንተን የሚገባቸው እነዚያው የመፅሀፉ ሰዎች (የስነመለኮት ሊቃውንት) ሲሆኑ እንደ አህመድ ዲዳት ያሉት መናፍቃን መጽሀፍ ቅዱስን በድፍረት እንደፈለጉ እያዛቡና እየጠመዘዙ በመተርጎም ሲያበላሹትና መቅኖ ሲያሳጡት ይታያሉ፣ ከባድ ጥፋት ነው፤ ቁርዓንን "ሰይጣናዊ ጥቅስ" ብሎ በድፍረት ከፃፈው ግለሰብ የማይተናነስ ብልግና ነው፤ በሃይማኖት መነቃቀፍ በህዝብ መካከል አለመረጋጋትንና መከፋፈልን (መለያየትን) ያመጣል፤ መለያየት ደግሞ የመጨረሻው ውድቀትን ያስከትላል፤ "እርስ ቦርሷ የምትለያይ መንግስት አትፀናም" ይላል፤ ማቴ12 ቁ.25።

አዘጋጁው፣

www.ethiopianorthodox.org

# መጽሐፍ ቅዱስና ሙሐመድ

## አይተዋወቁም

"መጽሐፍ ቅዱስ ስለሙሐመድ ምን ይላል ?" በሚል ርዕስ ሸህ አህመድ ዲዳት ላዘጋጀው ጥናታዊ ጽሑፍ የተሰጠ መልስ ነው ፡ ጥናቱ ያተኮረው ሙስሊሞች ነቢያችን ነው ስለሚሉት ስለሙሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተነገረ ትንቢት አለ ብለው ስለሚያምኑ የትንቢቱን እውነትነት ለማረጋገጥና በመረጃ የተደገፈ ጥናታዊ ጽሑፍ ለማቅረብ የተደረገ ጥረት ነው ።

የሃይማኖት መሪያችን የእውነት መምህራችን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ "በሐሰት አትማሉ ፡…ካለ በኋላ ነገር ግን ቃላችሁ አንድ ይሁን 'እመኒ እወ እወ ወእመኒ አልቦ አልቦ' ይህ ቃል በቃል ሲተረጎም "አዎን አዎን አይደለም አይደለም" ማለት ሲሆን ትክክለኛው አነጋገር እውነቱን እውነት ሐሰቱን ሐሰት በሉ ፡ ከነዚህ ከሁለቱ የወጣ ከሰይጣን ነው  ሲል ክርስቲያናዊ መመሪያ ሰጥቶናል ፡ ማቴ 5 ቁ 33–37 ፡ ስለዚህ እኛ ክርስቲያኖች ከመጽሐፉ ቃል ሳንወጣ ያለውን አለ ፡ የሌለውን የለም በማለት ሐቁን እንመሰክራለን ፡ እናረጋግጣለን ፡

መልሱን ከመስጠቴ በፊት ሸህ አህመድ ዲዳት ደቡብ አፍሪካዊ ቄስ ነው ከሚለው ሰው ጋር የተለዋወጡትን የመላምት ጥያቄና መልስ እንዳለ ጽፌ አቅርቤዋለሁ ፡ እንዳለ ያቀረብሁበት ምክንያት አንባቢዎች ጽሑፉን በሚከታተሉበት ጊዜ ጥያቄና መልሱን በቅርብ እንዲያገኙት ነው ፡ ከዚህም ሌላ ሸህ አህመድ በኦሪት ዘዳግም ምዕ 18 ቁ 18 ላይ ተመሥርቶ ከቄሱ ጋር ያካሄደው የመላምት አንፃራዊ ጥናት አንድ ወጥ በመሆኑ እኔም ለመልሱ ጣልቃ ሳልገባ ሳይሸራረፍ እንዲቀጥል ስለፈለግሁ በታዛቢነት በዳር ቆሜ ሁለቱ የሚሉትን ማዳመጥ መረጥሁ፡

ሸህ አህመድ መጽሐፍ ቅዱስን በአጽንኦት ተመልክቶታል ፡ በተለይ ሐዲስ ኪዳንን ደጋግሞ አንብቦታል ፡ በቃሉ ሸምድዶታል ፡ ይሁን

www.ethiopianorthodox.org

እንጂ አገላብጦ ቢያነበው ቢያነበንበው ስለመሐሙድ የተነገረ አንዳች ፍንጭ ሊያገኝ አልቻለም ፡ ሸሁ በዚህ ጥናት የዕድሜውን አጋማሽ እንዳሳለፈ ተናግሯል ፡ ምናልባት እንደመጽሐፉ ሰዎች ጠለቅ ያለ እውቀት ባይኖረኝ ይሆናል በማለት ስለተጠራጠረ ከመጽሐፉ ሰዎች ማለት ከቀሳውስትና ከሃይማኖት መሪዎች ጋር ቃል በቃል ለመነጋገርና ለመረዳት ወሰነ ፡ በዚህ ምክንያት አፍሪካዊ ቋንቋ ተናጋሪ ወደሆኑት አብያተ ክርስቲያናት ስልክ መደወል ይጀምራል ፡ ለጊዜው ግን የበጎ ፈቃድ መልስ ሊያገኝ አልቻለም ፡ በመጨረሻ ቫንኽርደን የተባለ ቄስ ሊያነጋግረው ፈቅዶ ቀጠሮ ያዘለት ፡ በተባለው ቀን በተያዘለት ቀጠሮ ሄዶ ከቄሱ ጋር ውይይት ይከፍታሉ ፡ በመጀመሪያ ሸህ አህመድ

"መጽሐፍ ቅዱስ ስለሙሐመድ ምን ይላል ?" ሲል ይጠይቃል ፡ ቄሱም ሳያመነታ "ምንም" ሲል ይመልሳል ፡ ሸህ አህመድ እንደገና "ለምን ምንም" መጽሐፍ ቅዱስ ስለሶቬት ሩሲያ አነሳስና ስለመጨረሻዎቹ ቀናት ከዚያም አልፎ ስለሮማ ካቶሊክ ጳጳስ ብዙ ነገሮችን እንደተናገረ ትተነትኑ የለም እንዴ ? ሲል ይጠይቃል ፡ ቄሱም "አዎ ፡ ስለሙሐመድ ግን ምንም የተነገረ ነገር የለም" ይላል ፡ እንደገና ሸህ አህመድ ኮስተር ይልና" ለምን ምንም ፡ ሙሐመድ እኮ ዓለማችንን ላጥለቀለቋት በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ምዕመናን መከሰት ምክንያት የሆኑና ከርሳቸውም በሆነ ትምህርት "ኢየሱስ በተአምራዊ መንገድ እንደተወለደ ፡ መሢህ እንደሆነ ፡ በአምላክ ፈቃድ ሙታንን እንዳስነሳ፣ ዕውር እንዳበራ፣ ለምፃሞችን እንዳነፃ የሚያምኑ ተከታዮችን ያፈሩ ሰው መሆናቸው የተረጋገጠ ነው ፡ ታዲያ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ኢየሱስና ስለእናቱ ማርያም በቀና መንፈስ ስለሚናገሩት ስለእኚሁ ታላቅ የሕዝቦች መሪ አንድ እንኳ የተናገረው ነገር የለም ?" ሲል ይጠይቃል ፡ ቄሱም ዕንግዳውን ቅር ላለማሰኘት ቃሉን አለሳልሶ "ልጄ መጽሐፍ ቅዱስን ላለፉት 50 ዓመታት ከማንበብ የቦዘንሁበት ጊዜ የለም ፡ እርሱን የሚጠቅስ ግን አንዳች ነገር ቢኖር ኖሮ ባወቅሁት ነበር" ሲል ስለሙሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተነገረ አንዳች ማስረጃ እንደሌለ በእውነት ያለሐሰት ይናገራል ፡



ሸህ አህመድ በረዥሙ ጊዜ ጥናቱ መጽሐፍ ቅዱስን በጥንቃቄ አገላብጦ አንብቦ ፡ ከዚያም የሃይማኖት መሪዎችን አነጋግሮ ያገኘው መልስ "መጽሐፉም ዝም ቄሱም ምንም" ስለሆነበት ተስፋ ቆርጦ "የወደዱትን ቢያጡ ያጡትን ይቀላውጡ" እንደሚባለው በዚህም በዚያም ተጨባጭ ማስረጃ ቢያጣ እንደገና ሌላ የመላምት ስልት ማፈላለግ ይጀምራል ።

## እንደሙሴ ያለ ነቢይ (እንደአንተ ያለ ነቢይ)

"በብሉይ ኪዳን ስለኢየሱስ መምጣት በመቶ የሚቆጠሩ ትንቢቶች የሉምን?" ሲል ሸህ አህመድ ለሚቀጥለው መላምቱ መግቢያ የሚሆነው ሌላ የመላምት ጥያቄ ለቄሱ አቀረበለት፡ "ቄሱም ምን በመቶ ብቻ በሺህ የሚቆጠሩ ትንቢቶች አሉ እንጂ" ሲል ይመልስለታል፡ ሸሁም… ከነዚህ በሺህ ከሚቆጠሩት ትንቢቶች ውስጥ ኢየሱስ በስም የተጠቀሰበትን ትንቢት ልታነብልኝ ትችላለህ? መሢሕ የሚለው ቃል መዓርግ እንጅ ስም አይደለም፡ የመሢሁ ስምስ ኢየሱስ ይሆናል የሚል ትንቢት አለ? … በንጉሡ በሄሮድስ ዘመን ኢየሱስ እንደሚወለድ የሚናገር ትንቢት አለን? ሲል ይጠይቃል፤ "ቄሱም እንዲህ ዓይነት ዝርዝር የለም" ሲል ይመልስለታል፤ "ታዲያ እኚህ በሺህ የሚቆጠሩ ትንቢቶች የኢየሱስን ስም የማይጠቅሱ ከሆነ እንዴት መደምደም ይቻላችኋል? ሲል ሸሁ ይጠይቃል፤ "ቄሱም ትንቢቶች ወደፊት የሚሆነውን ነገር የሚጠቁሙ የቃላት ሥዕሎች ናቸው፤ ያ ክስተት በገሃድ ደርሶ በተግባር ሲታይ አስቀድሞ የተነገረው መፈጸሙን ያስረዳል ሲል ይመልሳል፤ "እነዚያን በሺህ የሚቆጠሩ ትንቢቶች የበለትሃቸው በዚህ መንገድ ከሆነ ለምን እነዚህኑ መንገዶች ለሙሐመድ አንጠቀምባቸውም?" ሲል ሌላውን የመላምት ጥያቄ ያቀርብለታል።

"ቄሱም የቀረበው አሳብ መልካምና ለመወያየት የሚያስችል መንገድ እንደሆነ በዓይን ጥቅሻ የአወንታ መልስ "ከሰጠ በኋላ የያዘውን መጽሐፍ ቅዱስ ገልጦ ኦሪት ዘዳግም 18 ቁ·18 ያወጣል፤ ሸህ አህመድ አንቀጹን በቃሉ ያወቀው ስለነበረ "ከወንድሞቻቸው መካከል እንዳንተ ያለ ነቢይ አስነሳላቸዋለሁ፡ ቃሌንም ባአፉ አደርጋለሁ፡ ያዘዝሁትንም



www.ethiopianorthodox.org

ሁሉ ይነግራችኋል" የሚለውን በአፍሪካዊኛ ቋንቋ ካነበበለት በኋላ "ይህ ትንቢት ማንን ያመለክታል?" ሲል ቄሱን ይጠይቃል፤ ቄሱም "ቅንጣት ያህል ሳያመነታ "ኢየሱስን" ሲል ይመልስለታል፤ "ለምን ኢየሱስን?" የርሱ እኮ ስም ከዚህ አልተጠቀሰም" ቢለው "ትንቢቶች ወደፊት የሚሆነውን ነገር የሚገልጡ የቃላት ሥዕሎች እንደመሆናቸው መጠን በዚህ አንቀጽ የተነገሩት ቃላት እርሱን የሚገልጡ ናቸው፤ እንዳንተ ያለ ሲል እንደሙሴ ያለ ማለቱ ነው፤ ስለዚህ ኢየሱስ ከሙሴ ጋር ይመሳሰላል ይለዋል፤ እንዴት አድርጎ ነው ኢየሱስ ከሙሴ ጋር የሚመሳሰለው? ሲል ሸሁ ይጠይቃል፤ ቄሱም የሰጠው መልስ በመጀመሪያ ደረጃ ሙሴ አይሁድ ነበር፤ ኢየሱስም አይሁድ ነበር ፡ በሁለተኛ ደረጃ ሙሴ ነቢይ ነበር፤ ኢየሱስም ነቢይ ነበር፤ ስለዚህ ኢየሱስ ሙሴን ይመስላል፤ እግዚአብሔር ለሙሴ "እንዳንተ ያለ ነቢይ ብሎ የተነበየለት በትክክል ይህንኑ ነው" የሚል ነው፤ በሙሴና በኢየሱስ መካከል የምታስታውሰው ሌላ መመሳሰል አለን? በማለት ሸህ አህመድ እንደገና ቢጠይቀው ቄሱም ሌላ የሚያስታውሰው መመሳሰል እንደሌለ ያረጋግጥለታል።

በዘዳግም 18 ቁ· 18 ላይ በተገለጠው ትንቢት የታጨውን (ነቢይ) ለማግኘት መመዘኛዎቹ እነዚህ ሁለቱ ብቻ ከሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱት ሰዎች ሰሎሞን ኢሳይያስ ሕዝቅኤል ዳንኤል መጥመቁ ዮሐንስና የመሳሰሉትን መመዘኛው ይመጥናቸዋል ማለት ነው፤ ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ አይሁዶችም ነቢዮችም ነበሩና፤ ለምን ትንቢቱ ከነዚህ ነቢያት ላንዱ አልተሰጠም? ለምን ለኢየሱስ ብቻ ተሰጠው? ለምን አንዱን ብስል ሌላውን ጥሬ እናደርጋለን? በማለት ታጥቆ ለተነሳለት የፈጠራ መላምት ግንባር ላይ ዓይን ፈጥሮ ወገኖቹን ዕፁብ ድንቅ ለማሰኘት የተነሳው ሸህ አህመድ አምርሮ ይጠይቃል፤ ቄሱም ነገሩ ባይጥመውና ተቃውሞ ባያሰማም መልስ ግን ሊሰጥበት አልፈለገም፤ "አየህ! የእኔ መደምደሚያ ኢየሱስ ከሙሴ ጋር በእጅጉ አይመሳሰሉም የሚል ነው" በማለት ሸህ አህመድ የቄሱንም ምሳሌ ውድቅ አድርጎ የመጀመሪያው ውይይት በዚህ ይዘጋል፤ እኔም አሁን መድረኩ ክፍት ስለሆነ ተመልካችነቴ ቀርቶ ትክክለኛውን መልስ ለመስጠት መድረኩን ተረክቤአለሁ።

በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቱ ተስፋ የቆረጠው ሸህ አዲስ በፈጠረው መላ



www.ethiopianorthodox.org

ምት ቀደም ሲል ስለክርስቶስ የተነገሩትን ትንቢቶች የተመሰሉትን ምሳሌዎች ቢቻል ነጥቆ ባይቻል ሠርቆ ወስዶ ለሙሐመድ በማከናነብ ትንቢት የተነገረለት ነቢይ ለማሰኘት ነው፤ በብሉይ ኪዳን ስለኢየሱስ መምጣት በሺህ የሚቆጠሩ ትንቢቶች አሉ የሚል መልስ ቢሰጠው "እነዚህ ትንቢቶች እኮ የኢየሱስን ስም አልጠቀሱም፤ ታዲያ የኢየሱስን ስም የማይጠቅሱ ከሆነ ለምን ለሙሐመድ አንጠቀምባቸው?" ሲል የመላምት ጥያቄውን እንደዋዛ ጣል አደረገለት፤ ሸህ አህመድ እንደሚለው ቄስ የተባለውም ሰውዬ አሜን ብሎ ለድርድር መቅረቡ ከባድ ስህተት ነው፤ አንድ ሙስሊም ከመሬት ተነስቶ ስለክርስቶስ የተነገረውን ትንቢት የተመሰለውን ምሳሌ ለሙሐመድ እንጠቀምበት የሚል ጥያቄ ሲያቀርብለት እንዴት ሆኖ! እንዴትስ ተደርጎ! በማለት መቃወም ሲገባው አሜን ብሎ ቀምበር ማስጣሉ ከባድ ድክመት ነው፤ ቄስ መሆኑም ያጠራጥራል፤ ይህ ዓይነቱ ቄስ የክርስትናን ሃይማኖት መወከል የማይችል ተራ ሰው እንጂ የነገረ መለኮት ምሑር አይባልም ።

ፈረንጆች የአፍሪካን መሬት ቅኝ ግዛት ሲያደርጉ ሰዎችንም (አፍሪካውያኑንም) የሃይማኖት ቅኝዎች አድርገው በክርስቶስ ስም አጥምቀዋቸዋል እንጂ ስለነገረ መለኮት ጠለቅ ያለ እውቀት አላስጨበጧቸውም፤ ሸህ አህመድ ዲዳትም ለዚህ ተልካሻ መላምቱ መጠቀሚያ ሊያደርጋቸው የሚፈልጋቸው እንደነዚህ ያሉትን አዳዲስ ተክሎች ነው፤

የንጽጽሩ ጸሐፊ ከላይ የጠቀሰው ትንቢት ሙሉ ቃል እንደሚከተለው ይነበባል፡ "እግዚአብሔር አምላክህ ከወንድሞቻችሁ መካከል እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሳላችኋል፡ ነገሬን ባፉ አድርጋለሁ፡ ያዘዝሁትንም ቃል ሁሉ ይነግራችኋል፡ በስሜም የሚናገረውን ነገሬን የማይቀበለውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ፡ ነገር ግን በትዕቢት የሚዳፈር ነቢይ በስሜም የሚናገር ይናገር ዘንድ ያላዘዝሁትን ወይም በሌላ አምላክ ስም ቢናገር ያ ነቢይ ይሙት፡ በልብህ እግዚአብሔር ያልተናገረው መሆኑን አውቅ ዘንድ እንዴት ይቻለኛል? ብትል ይህች ምልክት ትሁንልህ፤ ያ ነቢይ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ ያው የተናገረው ባይደረግ ባይመጣም ይህ ነው እግዚአብሔር ያልተናገረው ነገር፡ ያ ነቢይ በድፍረቱ ተናገረው እንጅ፡ እርሱን አትፍራው" ይላል፡ ዘዳግም 18፡ 18—22፡ ዮሐ·1 ቁ·45 የሐዋ·ሥራ 7 ቁ·37፡

ትንቢቱን የተናገረው ነቢይ ሙሴ ነው፤ ንግግሩም እንዳንተ ያለ ነቢይ አይልም፤ እንደኔ ያለ ነው ያለው፤ ሙሴ እንደኔ ያለ ነቢይ ያለው ኢያሱን ነው፤ ኢያሱም የኢየሱስ ምሳሌ ነው፤ ነገር ግን ቄሱ ሙሴና ኢየሱስ በምን ይመሳሰላሉ? ተብሎ ቢጠየቅ ሙሴ አይሁድ ነበር፡ ኢየሱስም አይሁድ ነው፤ ሙሴ ነቢይ ነበር፡ ኢየሱስም ነቢይ ነው፤ ስለዚህ ኢየሱስ ሙሴን ይመስላል ሲል ከትንቢቱ ጋር የማይጣጣም መልስ ሰጥቷል፤ ኢየሱስ ነቢይ አይባልም፤ የነቢያት አምላክ ነው፤ ነቢይ ኢሳ የሚሉት ሙስሊሞች ናቸው።

ሙሴ "እንደኔ ያለ ነቢይ ያስነሳላችኋል" ብሎ ትንቢት ሲናገር ኢያሱ ገና ሕፃን (ብላቴና) ነበር፤ ለኢየሱስ ምሳሌ በመሆን እጩ ሆኖ የቀረበው ብላቴና ኢያሱ ከሙሴ ቀጥሎ የእስራኤል መሪ እንደሚሆን ባለመረዳት ሙሴና ኢየሱስ ይመሳሰላሉ ሲል ቄሱ የሰጠው መልስ የተሳሳተ ነው፤ እንግዲህ የትንቢቶችን መነሻና መድረሻ ጠንቅቆ ሳይረዱ አስተምራለሁ መልስ እሰጣለሁ ማለት ተሳስቶ ሌላውን ማሳሳት ነው ፡

ከላይ በተጠቀሰው ትንቢት ዝቅ ብሎ ቀድሞም የሐሰት ነቢያት እንደነበሩ እንረዳለን፤ "ነገር ግን በኩራት የሚደፍር ነቢይ በስሜም የሚናገር ይናገር ዘንድ ያላዘዝሁትን ወይም በሌላ አምላክ ስም ቢናገር ያ ነቢይ ይሙት፡ እግዚአብሔር ያልተናገረው መሆኑን አውቅ ዘንድ እንዴት ይቻለኛል? ብትል ይህች ምልክት ትሁንልህ፤ ያ ነቢይ በእግዚአብሔር ስም በተናገረ ጊዜ ያው የተናገረው ባይደረግ ባይመጣም ይህ ነው እግዚአብሔር ያልተናገረው ነገር፡ ያ ነቢይ በድፍረት ተናገረው እንጅ፡ እርሱን አትፍራው" ይላል፡ እንግዲህ ሽህ አህመድ ይህን ትንቢታዊ ማስጠንቀቂያ ሳይመለከተው ቀርቶ አይደለም፤ ይሁን እንጅ በድፍረት ረግጦት አልፏል፡ ድፍረት ደግሞ በሥጋ መቅሠፍትን በነፍስ ኩነኔን ያከናንባል።

ሙስሊሞች ነቢያችን ነው የሚሉት ሙሐመድ የእስልምና ሃይማኖትን አስፋፊልኝ ብሏቸው ይሆናል እንጅ ለኢየሱስ የተነገረውን ሀብተ ትንቢት ነጥቃችሁ ደርቡልኝ ይላቸዋል ብዬ አላምንም፤ ሀብተ ትንቢት ማንም ሊጋራው ወይም ሊነጥቀው የማይችል ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ሀብተ ፀጋ ነው፤ የዘመኑ ዲስኩረ ፀሐፊ ሽህ አህመድ ግን እስልምናን ለማስፋፋት ይጠቅመኛል ብሎ ይናገር ዘንድ ከእግዚአብሔር ያልታዘዘ



ውን ቀደም ሲል ስለመሲህ ክርስቶስ የተነገረውን ትንቢት በድፍረት ነጥቆ ለሙሐመድ ገጸበረከት ማቅረቡ ከባድ ኃጢአት ነው፡ እግዚአብሔር ይቅር ይበለው።

ሽህ አህመድ በሙሴና በኢየሱስ መካከል ሌላ መመሳሰል እንዳለ ቄሱን ጠይቆ ሌላ መመሳሰል እንደሌለ ከተረዳ በኋላ "እጩውን ለማግኘት መመዘኛዎች እነዚህ ሁለቱ ብቻ ከሆኑ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከተጠቀሱት ሰዎች ሰሎሞን ፡ ኢሳይያስ፡ ሕዝቅኤል፡ ዳንኤል፡ መጥመቁ ዮሐንስና የመሳሰሉትን መመዘኛው ይመጥናቸዋል፡ ምክንያቱም እነዚህ ሁሉ አይሁድም ነቢያትም ነበሩና፡ ለምን ትንቢቱ ከነዚህ ላንዱ አልተሰጠም? ለምንስ ለኢየሱስ ብቻ ተሰጠ? ለምንስ አንዱን ብስል ሌላውን ጥሬ እናደርጋለን?" ሲል ሀብተ ትንቢት ከሰው ወደሰው በችሮታው የሚተላለፍ ምድራዊ ፀጋ አስመስሎ አቅርቦታል፤ መቼም ሀብተ ትንቢት ከእግዚአብሔር የሚሰጥ ሰማያዊ ፀጋ እንጅ በማናለብኝነት በድፍረትና በጉልበት ነጥቆ የሚወሰዱት ተራ ነገር ባለመሆኑ ሙከራው ከምኞት አልፎ ውጤት ይኖረዋል ተብሎ አይታሰብም፤ ብቻ ያሳዝናል፡ ለዘብተኛው ቄስም ሙከራው አስገርሞት (አሳዝኖትም ሊሆን ይችላል) በድፍረት ለቀረበለት ጥያቄ መልስ ከመስጠት ተቆጥቧል፡ ስምዖን የተባለው ጠንቋይ መንፈስ ቅዱስን ከሐዋርያት በገንዘብ ሊገዛ በጠየቀ ጊዜ ቅዱስ ጴጥሮስ የእግዚአብሔርን ፀጋ በገንዘብ ልትገዛ አስበሃልና ብርህ ካንተ ጋር ይጥፋ ሲል ገሥፆታል፡ የሐዋ፡ሥራ 8፥ 18–33፡

## ሦስቱ አለመመሳሰሎች

ሽህ አህመድ ከላይ የተጠቀሰውን ትንቢት አስመልክቶ ከቄሱ ጋር እንደመግቢያ የተጠቀመበትን የንፅፅር መላምት ሲያጠቃልል "ኢየሱስ ከሙሴ ጋር በፍጹም አይመሳሰልም" ካለ በኋላ "በሙሴና በኢየሱስ መካከል ሶስት አለመመሳሰሎች አሉ፡ እንደእናንተ አባባል ኢየሱስ አምላክ ነው፡ ሙሴ ግን አምላክ አይደለም፡ ሁለተኛ እንደእናንተ አባባል ኢየሱስ ለዓለም ኃጢአት ቤዛ ሆኗል፡ ሙሴ ግን ለዓለም ኃጢአት ቤዛ መሆን አላስፈለገውም፡ ሦስተኛ እናንተ እንደምትሉት ኢየሱስ ለሶስት ቀናት ወደገሐነም (ወደመቃብር) ሄዶ ነበር፡ ሙሴ ግን ወደዚያ መሄድ አላስፈለገውም" ሲል ቄሱን ጠይቆት ቄሱም ለሁለቱ መመሳሰሎች

www.ethiopianorthodox.org

የአወንታ መልስ ሲሰጠው ለሶስተኛው ግን በቀዘቀዘ ስሜት አዎ ብለዋል ይላል፤ ፍጡርና ፈጣሪን ማወዳደር ከባድ ኃጢአት መሆኑ ቢታወቅም ሸህ አህመድ ሳይወድ በግድ የክርስቶስን አምላክነትና የበላይነት መስክ ሯል፡ ክርስቶስ የባሕርይ አምላክ ነው፡ ክርስቶስ የዓለም ቤዛ ነው፡ ክርስቶስ ዓርብ በሠርክ በአካለ ነፍስ ወደሲኦል ወርዶ ከአዳም ጀምሮ እስከርሱ የነበሩትን ነፍሳት ነፃ አውጥቷቸዋል፤ ክርስቶስ ወደ ገሐነም ወረደ አይባልም፤ ቂሱንም ቅር ያሰኘው ይህ ነው፤ ክርስቶስ ሶስት ቀን ሶስት ሌሊት በከርሠ መቃብር አድሮ በሶስተኛው ቀን ተነስቷል፤ ለሸህ አህመድ የማስተላልፈው መልዕክት አለኝ፡ ቂሱ ቢሳሳትም ለኢየሱስ ምሳሌ ሆኖ የቀረበው ኢያሱ መሆኑን እንተማመን፤ ለንፅፅሩ ግን ሙሴ ቢሆን ሌላ አልቃወም፤ ሸህ አህመድ እንደገና ዝቅ ብሎ የመላምቱን አድማስ በማስፋት ነቢያትን የሚሉትን መሐሙድን የንፅፅሩ ሶስተኛ ታዳሚ አድርጎ አቅርቦታል።

1ኛ· ሙሴ እናትና አባት ነበረው፡ ሙሐመድም እናትና አባት ነበሯቸው፡ ኢየሱስ ግን እናት እንጂ ሰብአዊ ፍጡር አባት አልነበረውም፤ ስለዚህ ኢየሱስ ሙሴን አይመስለውም፡ ሙሐመድና ሙሴ ግን ይመስ ላሉ።

2ኛ· "ሙሴና ሙሐመድ በተፈጥሮ ሕግ ከወንድና ከሴት ግንኙነት የተወለዱ ናቸው፡ ኢየሱስ ግን የተወለደው ልዩ በሆነ ተአምር ከእናት ብቻ ነው ፤ ማቴ· 1ቁ 18··· ስለዚህ ኢየሱስ ሙሴን አይመስለውም፡ ሙሴና ሙሐመድ ግን ይመሳሰላሉ።"

3ኛ· "ሙሴና ሙሐመድ አግብተው ወልደዋል፡ ኢየሱስ ግን በመላ ሕይወቱ አላገባም፡ ስለዚህ ኢየሱስ ሙሴን አይመስለውም፡ ሙሐመድና ሙሴ ግን ይመሳሰላሉ" ብሏል የንፅፅሩ ጸሐፊ ፤ እነዚህ ከ1–3 ተራ ቁጥር የተዘረዘሩት መላምቶች ተመሳሳይ በመሆናቸው አንድ ዓይነት መልስ ነው የሚያስፈልጋቸው፡ ለንፅፅር ይጠቅሙኛል ብሎ ያቀረባቸው እነዚህ መላምቶች የክርስቶስን አምላክነትና የበላይነት ከሚያረጋግጡ በስተቀር የንፅፅሩን ጸሐፊ የሚጠቅሙ አይደሉም፡ ለንጽጽሩ የቀረቡት ግለሰቦች ፍጡራን እንደመሆናቸው መጠን ጽድቅም ኃጢአትም ይስማማቸዋል፡ ክርስቶስ ግን የባሕርይ አምላክ ስለሆነ ጽድቅ እንጅ ኃጢአት እውነት እንጅ ሐሰት አይስማማውም፡ በዚህ ዓለም ላይ ሰዎች የሆኑትን ሁሉ



መሆን አያስፈልገውም።

4ኛ· "ሙሴና ሙሐመድን በሕይወት ሳሉ ሕዝቦቻቸው በነቢይነታ ቸው ተቀብለዋቸዋል፡ አይሁዳውያን በሙሴ ላይ ችግር መፍጠራቸውና ማጉረምረማቸው ባይካድም በኋላ ግን ሙሴ ለነርሱ የተላከ የእግዚአብ ሔር መላክተኛ መሆኑን አምነው ተቀብለዋል፤ አረቦችም የሙሐመድን ሕይወት ክፉኛ ተፈታትነውታል፡ ሥቃይና መከራ አድርሰውባቸዋል፤ ከተወለዱባት ከተማ ከመካ አሰድደዋቸዋል፡ በኋላ ግን መላው የዓረብ አገር የአላህ መላክተኛ መሆናቸውን ተቀብሎታል፤ በአንፃሩ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚነግረን "ኢየሱስ ወደወገኖቹ መጣ፡ ወገኖቹ ግን አልተቀበ ሉትም" ይላል፡ ዮሐ· 1ቁ11፡ ዛሬም ቢሆን ከ2000 ዓመታት በኋላ ወገኖቹ አይሁድ በሙሉ አልተቀበሉትም፡ ስለዚህ ኢየሱስ ሙሴን አይመስልም፡ ሙሐመድ ግን ሙሴን ይመስላሉ" ብሏል።

የእስራኤል ሕዝብ ቅምጥል (ምርጥ ሕዝብ) በመሆኑ እንኳን በሙሴ ላይ በእግዚአብሔር ላይ ያጉረመርም ነበር ፡ እግዚአብሔርም አንዳንድ ጊዜ ጠላት እያስነሳ ያለዚያም በልዩ ልዩ መቅሠፍት ይቀጣቸው ያሸቆጠቁጣቸው ነበር ፤ ሙሐመድም ሃይማኖቱንና ነቢይነቱን የሜነባ ቸው ታሪኩ እንደሚያስረዳው ወገኖቹ ዓረቦችን እንደበርሀ ግመል በጦር ኃይል አምበርክኮ ነው እንጅ አስወድዶና አስፈቅዶ እንዳልነበረ ይታወ ቃል ፤ ክርስቶስ ግን ወንጌልን በሚያስተምርበት ጊዜ ጥቂት የአይሁድ ካህናት ሕጋቸውን የሚለውጥባቸውና ጥቅማቸውን የሚነካባቸው ስለመ ሰላቸው ለጊዜው ቢቃወሙትም በልዩ ልዩ ተአምራት አምላክነቱን እየገለጠ በማስተማሩ በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ ማኅበረ አይሁድ አምነው ተቀብለውታል ፤ ቀያፋ የተባለው የካህናት አለቃ "እነሆ ዓለም ሁሉ ተከተለው ፡ ዓለም ሁሉ እርሱን ተከትሎ ከሚጠፋ አንድ ሰው ብንገድል ይሻላል" ሲል አስተያየቱን ሰጥቷል ፤ ባንድ በኩል ክርስቶስን የተከተለው ሕዝብ እጅግ ብዙ እንደነበረ ሲያረጋግጥ በሌላ በኩል ደግሞ ዓለም በኃጢአት ከሚጠፋ ስለዓለሙ ኃጢአት ክርስቶስ ይሙት ሲል ትንቢት መናገሩ ነው ፤ ዮሐ· 11 ቁ50–52 ።

የክርስቶስ አምላክነትና መድኃኒትነት በይበልጥ ሊታወቅ የቻለው ክርስቶስ ከሞተ በኋላ በደቀ መዛሙርቱ በሐዋርያት ስብከትና ከፍተኛ

www.ethiopianorthodox.org

መሥዋዕትነት ነው ፣ የሐዋ ሥራ 2 ቁ 41 ፣ የሐዋ ሥራ 4 ቁ 4 ተመልከት፣

5ኛ. "ሙሴና ሙሐመድ ነቢያትም ነገሥታትም ነበሩ… ሙሴ እንደንጉሥ ሕዝቡን ይቀጣ ይሠራ ነበር ፣ ዘኁልቁ 15 ቁ 36 ተመልከት ፣ ሙሐመድም በሕዝባቸው ሕይወትና ንብረት ላይ ሞትና ቅጣት የመወሰን ሥልጣን ነበራቸው ፣ ….. ኢየሱስም በዓመፅ አነሳሽነት ተወንጅሎ ከሮማው ገዥ ጴንጤናዊው ጲላጦስ ፊት በቀረበበት ወቅት የሐሰት ውንጀላውን ለማስተባበል አሳማኝ የመከላከያ አሳብ አቅርቦ ነበር ፣ "መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም ፣ መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን ኖሮ ለአይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ /መላዕክት/ በተዋጉልኝ ነበር ፣ ነገር ግን መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም ብሏል ፤ ዮሐ 18 ቁ 36፣ ጲላጦስም ኢየሱስ የሚፈልገው መንፈሳዊ መንግሥትን (ነቢይነትን) እንጂ ምድራዊ መንግሥትን የማይፈልግ መሆኑን አረጋገጠ ፣ ስለዚህ ኢየሱስ ሙሴን አይመስልም ፣ ሙሐመድ ግን ሙሴን ይመስላሉ" ብሏል።

የሙሴ ነቢይንትና መሪነት አያከራክርም ፣ ዓለም ያወቀው ፀሐይ የሞቀው ነው ፤ እግዚአብሔር ሙሴን ወደደብረሲና ጠርቶ ቃል በቃል እያነጋገረ ሕገ መንግሥቱን (አስሩን ትዕዛዛት) ሰጥቶ በእስራኤል ላይ መሪ ነቢይ (ቆራጭ ፈላጭ ሹም) አድርጎታል ፤ ሙሐመድ ግን እኔ የአላህ መላክተኛ ነኝ ፣ አላህ በዋሻ ውስጥ (በተራራ ላይ) አነጋገረኝ ሲል ከማስታወቁ በስተቀር እንደሙሴ በሕዝብ ፊት በማስረጃ የተደገፈ ታሪክ አላቀረበልንም ፣ በረመዳን ወር ባንድ ዋሻ ውስጥ ሳሉ በመልአኩ በገብርኤል አማካይነት "አንብብ አንብብ" አላቸው ፣ ማንበብ አልችልም ቢሉ መልአኩ ደጋግሞ አዘዛቸው ይላል ፤ ቁርዓን 96 ቁ.1–5 ፣ ኢየሱስ ግን በጲላጦስ ፊት ለፍርድ በቀረበ ጊዜ አንተ የአይሁድ ንጉሥ ነህ? ብሎ ቢጠይቀው አንተ ከልብህ አስበህ ተናገርህ? ወይስ ሌሎች ስለ እኔ ነገሩህ? ካለ በኋላ … መንግሥቱ ከዚህ ዓለም አይደለችም ፣ መንግሥቴስ ከዚህ ዓለም ብትሆን ኖሮ ለአይሁድ እንዳልሰጥ ሎሌዎቼ መላእክት በተዋጉልኝ ነበር ፤ ነገር ግን መንግሥቴ ከዚህ ዓለም አይደለችም በማለት ወደዚህ ዓለም የመጣው የዕንቁ ዘውድ ጭኖ ሕዝብን አሕዛብን ለመምራትና ለማስተዳደር ሳይሆን በመስቀል ዙፋን ላይ የሾህ አክሊል ደፍቶ ሥጋውን



ቆርሶ ደሙን አፍስሶ ሕዝብን አህዛብን ለማዳን እንደሆነ አምላክነቱንና መድኃኒትነቱን/ባደባባይ አስረድቷል ዮሐ.18 ቁ36 ፣

6ኛ. "ሙሴና ሙሐመድ" ለሕዝባቸው አዳዲስ ሕጎችንና መመሪያ ዎችን አውጥተዋል ፣ ሙሴ ለእስራኤል አስሩን ትዕዛዛት ከመስጠቱም በላይ የእምነት ሥርዓት ደንቦችንና መመሪያዎችን ደንግጓል ፣ ሙሐመ ድም እጅግ ኋላቀር በሆነ የድንቁርና አምልኮ ባዕድ ተዘፍቆ ይኖር የነበረውን ሕዝባቸውን መንጥቀው ነፃ ከማውጣታቸውም ባሻገር ዓረቦች ከዚያ በፊት አይተውትና ሰምተውት የማያውቁትን ሕግና ሥርዓት አውጥተውላቸዋል ፣ ኢየሱስን በተመለከተ አይሁድ ሕጋቸውንና ትምህ ርታቸውን የሚለውጥባቸው ስለመሰላቸው ያደረባቸውን ጥርጣሬ ለማስወ ገድ "እኔ ኦሪትንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽማ ቸው ነው እንጅ ፣ እውነት እላችኋለሁ ፣ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት የወጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ" ብሏል ፣ ማቴ. 5 ቁ 17 ባጭሩ ኢየሱስ እንደሙሴና እንደመሐመድ አዲስ ሕግና አዲስ ሃይማኖት አልፈጠረም ፤ ስለዚህ ኢየሱስ ሙሴን አይመስልም ፣ ሙሐመድ ግን ሙሴን ይመስላሉ ተብሏል።

የሙሴ ሕግ አውጭነትና ሕግ አስፈጻሚነት አያጠራጥርም ፣ አያከራክርም ፣ የሞራል የሃይማኖት የመንግሥትና የሕዝብ ሕጎች ደንቦችና መመሪያዎች ሁሉ ምንጫቸው የሙሴ ሕግ ነው ፤ ለማስረጃ ያህል "እግዚአብሔር አምላክህን አምልክ ፣ አትግደል ፤ አትስረቅ ፣ አታመንዝር ፣ እናትና አባትህን አክብር ፣ በሐሰት አትመስክር ፣ ባልንጀራህን እንደ ራስህ ውደድና … የመሳሰሉት ናቸው ፣ ዘፀዓት 20 ቁ1–16 ፤ ሙሐመድ ግን አንድ አምላክን ሰበከ (ሃይማኖትን አስተማረ) እንጅ ሕግና ሥርዓትን አላወጣም ፤ ጠጭነት አመንዝራነት አምልኮ ባዕድና ሌሎችም የሞራል ውድቀት የሚያስከትሉ ድርጊቶች ሁሉ በሙሴ ሕግ (በኦሪት) ቀደም ሲል የተከለከሉ ናቸው ፤ ኢየሱስ አዲስ ሕግ አዲስ ሃይማኖት አላወጣም የተባለው መላምት ግን ፈር የለቀቀ ክህደት ነው ፣ "የቄስ ሚስት ሠለጠነች ቢሏት መጽሐፍ አጠበች" ይባላል፤ ሸህ አህመድ



www.ethiopianorthodox.org

በድፍረት በሚያቀርባቸው መላምቶች በወገኖቼ ሙስሊሞች ዘንድ ተደንቆባቸውና ተሸልሞባቸው ይሆናል ፤ እስካሁን ያቀረባቸው መላም ቶች ትክክለኞች ናቸው ባይባሉም ያሁኑ ግን ግልጥ ክህደት ነው ፡ እንዴት ክርስቶስ አዲስ ሕግ አዲስ ሃይማኖት አላመጣም ይባላል? ይህ የራስን ሕልውና እንደ መካድ ይቆጠራል ፤ ቁርዓን በብዙ ቦታ ላይ ተውራት (ኦሪት) ለሙሴ ፡ እንጅል (ወንጌል) ለኢሳ ተሰጥተዋል እያለ ያውጃል ፤ በሌላም ስፍራ እናንተ የመጽሐፉ ሰዎች ማለት ኦሪትና ወንጌል የተሰጣ ችሁ አይሁድና ክርስቲያኖች ናቸው ይላል ፡ ታዲያ ሌላው ቀርቶ ቁርዓኑን መካድ አይደለምን?

ኢየሱስ "ኦሪትንና ነቢያትን ልሽራቸው አልመጣሁም ልፈጽማ ቸው እንጂ" ማለቱ አዲስ ሕግ አዲስ ሃይማኖት አላመጣሁም ማለቱ አይደለም ፡ ኢየሱስ አምላክ እንደመሆኑ መጠን የኦሪትም ጌታዋ ፈጣሪዋ ነው ፤ ቀደም ሲል በደብረሲና በኅቡዕ ሙሴን ቃል በቃል እያነጋገረ ሕገ ኦሪትን የሰጠ ፡ በኋላም ከድንግል ማርያም ተወልዶ ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ አዲስ ኪዳንን (ሕገ ወንጌልን) ያስተማረ የደነገገ ፡ አዲስ ሃይማኖት ክርስትናን የመሠረተ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው ።

ኦሪትንና ነቢያትን ልሽር አልመጣሁም ማለቱ ክርስቶስ ሕግ አውጭ እንደመሆኑ መጠን ቀደም ሲል የነበረውን የኦሪቱን ሕግ ፈጽሞ አልሻረባቸውም ፤ ለማስረጃ ያህል "ለቀደሙት ሰዎች በኦሪት አትግደል የተባለውን ሰምታችኋል ፡ እኔ ግን እንኳን የገደለ በወንድሙ ላይ በከንቱ የተቆጣ (ወንድሙን የሰደበ) በፍርድ ይፈረድበታል እላችኋለሁ ፤ … ለቀደሙት ሰዎች በኦሪት አታመንዝር የተባለውን ሰምታችኋል ፡ እኔ ግን እንኳን ያመነዘረባት ወደ ሴት አይቶ የተመኛት ፈጽሞ በልቡ አመነዘረ ባት እላችኋለሁ ፡… ለቀደሙት ሰዎች ዓይን ቢጠፋ ዓይን ይጥፋ ፡ ጥርስ ቢሰበር ጥርስ ይሰበር የተባለውን ሰምታችኋል ፤ እኔ ግን እላችኋለሁ ፤ ክፉውን በክፉ አትቃወሙ ፡ ነገር ግን" ቀኝ ፊትህን ቢመታህ ግራ ፊትህን አዙረህ ስጠው ፤ ቀሚስህን ለወሰደብህ መደረቢያህን ጨምርለት፡ ለቀደሙት ሰዎች ወዳጅህን ውደድ ጠላትህን ጥላ የተባለውን ሰምታች



www.ethiopianorthodox.org

ኋል ፡ እኔ ግን ጠላቶቻችሁን ውደዱ የሚረግሟችሁን መርቁ ፡ ለሚጠሏች ሁም መልካም አድርጉ ፡ ስለሚበድሏችሁና ስለሚያሳድዷችሁ ሰዎች ጸልዩ" ይላል ፤ ማቴ·5ቁ· 21–44 ተመልከት ።

የሙሴ ሕግ አውጭነት ከክርስቶስ ሕግ አውጭነት በመሠረቱ ይለያያል ፤ ሙሴ ሕገ ኦሪትን ሲደነግግ እግዚአብሔር በቃል ያዘዘውን እግዚአብሔር እንዲህ ብሏል እያለ ነው ይጽፍና ያስተምር የነበረው ፤ ክርስቶስ ግን ሕግ አውጭ ሕግ ተርጓሚና ሕግ አስፈጻሚ እንደመሆኑ መጠን የቀድሞው ሕግ እንዲህ ብሎ ነበር ፡ እኔ ግን እንዲህ እላችኋለሁ እያለ እንደታላቅ ባለሥልጣን ያስተምራቸውና አመራር ይሰጣቸው ነበር፡ ይህን በማድረጉም አንተ ማነህ? አንተ ከሙሴ ትበልጣለህ? ብሎ የተቃወመው ሰው አልነበረም ፤ ስለዚህ ክርስቶስ የሁለቱ ሕጎች ማለት የሕገ ኦሪትና የሕገ ወንጌል ባለቤት እንደመሆኑ መጠን በሕግ አውጭነቱ በሕግ ተርጓሚነቱና በሕግ አስፈጻሚነቱ ሙሴም ሆነ መሐመድ ፍጡራን ስለሆኑ ሊወዳደሩት አይችሉም ፤ ስለዚህ ኢየሱስ አዲስ ሕግ አዲስ ሃይማኖት አላመጣም ብሎ ፓንፍሌት መርጨት የራስን ሕልውና ጭምር መካድ ስለሆነ ሙስሊሙ ሕብረተሰብም ሸህ አህመድን አበጀህ አቤ (ጎሽ) የሚለው አይመስለኝም ።

7ኛ/ "ሙሴም ሆነ ሙሐመድ የተፈጥሮ ሞትን ሞተዋል ፡ የክርስትና ሃይማኖት እንደሚነግረን ከሆነ ግን ኢየሱስ አሰቃቂ በሆነ አሟሟት በመስቀል ተቸንክሮ ሞቷል ፤ ከዚሁ አንፃር ኢየሱስ ሙሴን እንደማይመ ስል ሙሐመድ ግን ሙሴን እንደሚመስሉ የተረጋገጠ ነው" ተብሏል ።

ሙሴና ሙሐመድ ፍጡራንና ኃላፍያን እንደመሆናቸው መጠን የማይቀረውን የሞት ጥዋ ተጎንጭተዋል ፤ የክርስቶስ ሞት ግን የተፈጥሮ ሞት አይደለም ፡ በሰውና በእግዚአብሔር መካከል ሲጠበቅ የኖረ ሌሎችን የማዳን ኃይል ያለው ዘላለማዊ ሕይወት ነው ፤ አዳምና ሔዋን አትብሉ የተባሉትን ዕፀ በልተው በዚህ ምክንያት የአዳም ዘር ሁሉ የሞት ሞት ተፈርዶበት የነበረውን የኃጢአት ፍርድ ራሱ ተቀብሎ ብዙኃኑን ስለማዳን መከራው እጥፍ ድርብ ሆነ ፤ የብዙኃኑን ሞት በመስቀል ላይ ጠረቀው (ቸነከረው) ሞቱና ስቅለቱ ሲጠበቅ የኖረ ስለመሆኑ ቀደም ሲል

ነቢዩ ኢሳይያስ "በእውነት እርሱ ደዌአችንን ወሰደ ፡ ሕማማችንን ተሸከመ ፡ እኛም እንደተመታ ቆጠርነው ፡ እግዚአብሔር እንደቀሰፈው እንደተዋረደም ፡ እርሱ ግን ስለኃጢአታችን ተወጋ ፡ ስለአመፃችንም ተደቀቀ ፡ የደህንነታችን ተግሣፅ በርሱ ላይ ነው ፡ በርሱ ቁስል እኛ ተፈወስን ፡ እኛ ሁላችን እንደ በግ ጠፋን ፡ ሁሉ ወደ መንገዱ አዘነበለ ፡ የሁላችንንም ኃጢአት እግዚአብሔር በርሱ ላይ አኖረበት ፡ ተጨነቀ ተሠቃየም ፡ አፉንም አልከፈተም ፡ እንደ በግ ወደመታረድ ሄደ ፡ እንደጠቦትም በሸላቹ ፊት ዝም አለ ፡ አፉንም አልከፈተም" ሲል ትንቢት ተናግሯል ፤ ኢሳ· 53 ቁ· 4–7 ተመልከት።

መጥምቁ ዮሐንስም በዮርዳኖስ ማዶ እያስተማረና የንስሐ ጥምቀት እያጠመቀ ሲሄድ ኢየሱስ ወደርሱ ሲመጣ አይቶ "እነሆ የእግዚአብሔር በግ የዓለሙን ኃጢአት የሚያስወግድ" ሲል የዓለም መድኀኒትነቱን አረጋግጦ መስክሯል ፤ ዮሐ· 1 ቁ· 29 ።

"ክርስቶስ ደግሞ አንድ ጊዜ ስለኃጢአተኞች ሞቷልና ፡ ጻድቁ ስለዓመጸኞች ፡ እኛን ወደ እግዚአብሔር ያቀርበን ዘንድ በሥጋው ሞተ ፡ በመንፈስ (በመለኮት) ግን ሕያው ነው ፡ በርሱ (በመለኮት) በግዞት ወዳሉት ነፍሳት ሄደ ፡ ሰበከላቸውም" 1 ጴጥ·3 ቁ·18–19 ።

ስለዚህ የክርስቶስ ሞት እንደሙሴና እንደ ሙሐመድ የተፈጥሮ ሞት ሳይሆን አዳምና ልጆቹ 5500 ዘመን ሲጠብቁት የኖረ ዛሬም ነገም ሞቱንና ስቅለቱን አምነው ለሚቀበሉት ሁሉ ዘላለማዊ ቤዛ ነው ፤ "በእግዚአብሔርና በሰው መካከል ያለው አንድ ነው ፡ እርሱም ሰው የሆነው ክርስቶስ ኢየሱስ ፤ ራሱን ለሁሉ ቤዛ የለወጠ ፤ ምስክርነቱም በጊዜዋ የመጣች "1ኛ ጢሞ· 2 ቁ· 5 ተመልከት ።

8ኛ/ "ሙሴም ሆነ ሙሐመድ በመሬት ላይ በመቃብር አርፈዋል፤ እናንተ እንደምትሉት ከሆነ ግን የሰው ልጅ (ክርስቶስ) በእግዚአብሔር ኃይል በቀኙ ተቀምጧል" ይላል፤ ሉቃ· 22 ቁ· 69 ፤ እንግዲያውስ ኢየሱስ ሙሴን አይመስልም፤ ሙሐመድ ግን ሙሴን ይመስላሉ" ተብሏል፤

ከዓቅም በላይ መንጠራራት ወደ ኋላ (የእንግላል) መውደቅን ያስከትላል፤ "የልጅ ተሚጋች በፊት ሰማይ ሰማይ ኋላ መሬት መሬት"



ይባል የለምን? ሸህ አህመድ ከዓቅም በላይ ፍጡርና ፈጣሪን አነፃፅራለሁ ብሎ በመጨረሻ በጠቀሰው ኃይለ ቃል ተረትቷል ተመትቷል ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሁሉ በላይ ፈጣሪ መሆኑን አረጋገጠ፤ ከማን አንሼ የሚደረግ የሃይማኖት ሙግት (ሃይማኖታዊ ንፅፅር) ቢቀር ምን አለበት? ደግሞስ እያወቁ ማጥፋት ማንን ለመጥቀም ነው? ወይስ ማንን ለመጉዳት? ክርስቶስ ሳውልን በተሳለ ስለት ላይ ብትቆም ራስህን ትጐዳለህ ነው ያለው ፡ የሐዋ· ሥራ 9 ቁ·1-5–ወልድ ክርስቶስ ከአብ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ዓለምን የፈጠረ የባሕርይ አምላክ መሆኑን እያወቅን ባንቀበለው ራሳችንን እንጎዳለን እንጂ ክርስቶስ አይጎዳም፤ የሐዋ· ሥራ 9ቁ·1–5 ፤

እነዚህ ከ1–8 ተራ ቁጥር የተዘረዘሩት መላምቶች (አለመመሳሰሎች) የክርስቶስን አምላክነት ከሚያረጋግጡ በስተቀር በክርስትና ሕይወት ላይ የሚያደርሱት ሹሉታዊ ተፅዕኖ የለም፤ እኛ ክርስቲያኖች እንደምናምነው ሸህ አህመድም እንደአረጋገጠው ክርስቶስ ከማንም ጋር ሊመሳሰል የማይችል የባሕርይ አምላክ ነው፡ ክርስቶስ ከማንም ጋር የማይመሳሰል የባህርይ አምላክ በመሆኑ ሸህ አህመድ ሳይታወቀው እግዚአብሔር አፉን ከፍቶ ፊቱን ጸፍቶ የበላይነቱን እንዲመሰከር አድርጎታል ፤ እግዘአብሔር ከፈለገ እንኳን በመልኩ በአምሳሉ የፈጠረውን ሰው የበለዓም አህያና የቢታንያ ድንጋይ በሰው አንደበት እንዲናገሩ አድርጓል፤ ኦሪት ዘኁልቁ 22 ቁ· 28–30፡ ሉቃ· 19 ቁ· 38–40፤ ማን ያውቃል? ይዋል ይደር እንጂ ሸህ አህመድም አንድ ቀን የክርስቶስ ደቀ መዝሙር ሆኖ የዓረቡን ዓለም እንደሚሞግተው አልጠራጠርም።

ከዚህ በላይ ሸህ አህመድ ዲዳት በክርስትና ሕይወት ላይ እያነጣጠረ የተኮሳቸው ስምንት የፈጠራ መላምቶች እንደዘመኑ መሣሪያ (እስኬድ ሚሳይል) ኢላማቸውን ሳይመቱ በዓየር ላይ እርስ በርሳቸው እየተላተሙ (እየተጋጩ) መክነው እንዲቀሩ ተደርገዋል፤ በክርስትና ሕይወት ላይ ያደረሱት አንዳች ጉዳት የለም።

ሸህ አህመድ ቀደም ሲል ለቄሱ ያቀረበለት ጥያቄ "መጽሐፍ ቅዱስ ስለሙሐመድ ምን ይላል?" የሚል እንደነበረ እናስታውሳለን፤ ቄሱም የሰጠው መልስ "ሙሐመድ በመጽሐፍ ቅዱስ ምንም ዕውቅና የለውም" የሚል የማያዳግም እንደነበረ አይዘነጋም፤ እንደገናም ተስፋ የማይቆርጠው ሸህ አህመድ አዲስ የፈጠራ መላምት አዘጋጀለት፤ ቄሱም ድንገት

www.ethiopianorthodox.org

ሳያስበው ተቀነባብሮ ለቀረበለት የመላምት ጥያቄ.የሆነ ያልሆነውን እየቀባጠሩ መልስ ከመስጠት የአወንታ ገጽታ እያሳዩ መጨረሻውን ማየት እንደመረጠ ተመልክተናል፡ ምክንያቱም ቄሱ ከ3000 ዓመት ዓለም በፊት ስለመሲሕ ክርስቶስ መምጣት የተነገረውን ትንቢት ለእኛ ይገባል የሚል ተፋላሚ ይነሳል ብሎ ሊያስብና ሊጠረጥር አይችልም፡ ጥያቄው ለማንም ዱብዕዳ ነው፡ አሁንስ ይህ ይሆናል ብሎ ማን ይገምታል? የቸገረው ርጉዝ ያገባል፤ ልጁ ሲወለድ ግን አባቱ ሌላ ነው።

ቄሱ ድክመት የለበትም ማለት አይደለም፤ ለክርስቶስ ምሳሌ ሆኖ ትንቢት የተነገረለት ኢያሱ ሲሆን ሙሴና ኢየሱስ ምሳሌ ናቸው ብሎ ማስረዳቱ ከባድ ስህተት መሆኑን ተናግሬያለሁ፤ "እንደኔ ያለ ነቢይ ያስነሳላችኋል" ተብሎ በሙሴ የተነገረው ትንቢት ለጊዜው ለኢያሱ ሲሆን ፍጻሜው ግን ለክርስቶስ መሆኑ መታወቅ አለበት፤ ትንቢቱን ለማረጋገጥ ወንጌላዊው ዮሐንስ የጻፈውን እንመልከት፤ "ፊልጶስ ናትናኤልን እንዲህ አለው "ሙሴ ስለርሱ በኦሪት የጻፈለትን መሲህ ክርስቶስ አገኘነው፡ እርሱም ኢየሱስ የናዝሬቱ የዮሴፍ ልጅ" ይላል፤ ዮሐ· 1 ቁ·46፤ ዘዳግም 18 ቁ· 18 የሐዋ· ሥራ 7 ቁ·37፤

የክርስቶስ አመጣጥ ከላይ እንደተገለጠው ትንቢት ተነግሮለት ምሳሌ ተመስሎለት ነው እንጂ ዕንግዳ ደራሽ ውሃ ፈሳሽ አይደለም፤ ትንቢት ሰምና ወርቅ ነው፡ አንጥረኛ ወርቅን ለማፍሰስ አስቀድሞ የሚፈልገውን ዓይነት ፎርም (ቅርፅ) በሰም ያዘጋጃል፤ ወርቁ ከፈሰሰ በኋላ ሰሙ ፈጋፊ (ቀሪ) ነው ፡ ወርቁ ግን የሰሙን ሥፍራ ይዞ ነባራዊ ይሆናል፡ ኢያሱ ሰም ሲሆን <u>ኢየሱስ ግን ነባራዊ ወርቅ ነው፤</u>

እያሱ ኢየሱስን በሁለት ነገር ይመስለዋል፤ አንደኛ ኢያሱ ማለት መድኃኒት ማለት ነው፡ ኢየሱስም ማለት መድኃኒት ማለት ነውና፤ ሁለተኛ ኢያሱ የእስራኤልን ሕዝብ እየመራ ወስዶ ምድረ ርስትን አውርሷቸዋል፡ ኢየሱስም በስሙ ያመኑ የተጠመቁትን ምዕመናን (ክርስቲያኖችን) ሰማያዊት ርስት ገነትን (መንግሥተ ሰማያትን) አውርሷቸዋልና።

## የሙሴና የኢያሱ አጭር ታሪክ

ሙሴና ኢያሱ በተከታታይ ታላቁን የእግዚአብሔርን ሕዝብ እሥራኤልን በሚያስደንቅና በሚያስገርም አኳኋን የመሩና ያስተዳደሩ ነቢያትና



www.ethiopianorthodox.org

መሳፍንት ናቸው፤ የሁለቱንም መሪዎች አስደናቂ ታሪክ ባጭሩ እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

ሙሴ በእግዚአብሔር ጥበብ የፈርዖን የልጅ ልጅ እየተባለ በፈርዖን ቤተመንግሥት ተቀማጥሎ ያደገ እስራኤላዊ ነው፤ በኋላም እግዚአብሔር ባወቀ ላንድ ታላቅ ተልዕኮ አዘጋጅቶታልና ባንዲት ትንሽ ምክንያት ከግብፅ ውጭ ወደ ምድያም አገር እንዲሰደድ አደረገው፤ ሙሴ አርባ ዘመን ሲሆነው በምድያም የአማቱን በጎች ሲጠብቅ እግዚአብሔር በቁጥቋጦ አምሳል ተገልጦ ወደ ግብፅ ወርደህ ሕዝቤን እስራኤልን ከፈርዖን እጅ ነፃ አውጣ አለው፡ ሙሴም እኔ ማነኝ? እስራኤልን ነፃ አወጣ ዘንድ በዚህ ላይ አንደበቴ ልቱት ነው አለው፡ ሂድ አትፍራ፤ እኔ እግዚአብሔር የእስራኤል አምላክ ነኝ፡ የፈርዖን አምላክ አድርጌሃለሁ ፡ አንተ ለወንድምህ ለአሮን ንገረው፡ አሮን ደግሞ ለፈርዖን ይንገረው አለው፤ አንተን ምክንያት አድርጌ በፈርዖን ላይ ኃይሌን እገልጣለሁ ማለቱ ነው፤ ከዚህ በኋላ ሙሴ ወደ ግብፅ ወርዶ እግዚአብሔር ወገኔን እስራኤልን ልቀቅ ብሎ አዟል ሲል ለፈርዖን ነገረው፤ ፈርዖንም እሺ እል ዘንድ እስራኤልንም እለቅ ዘንድ እግዚአብሔር ማነው? እግዚአብሔርን አላውቅም፤ እስራኤልንም አለቅም አለው፡ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት ንጉሥ ፈርዖንንና ግብፃውያንን በልዩ ልዩ መቅሰፍት አስጨንቆ ወገኖቹን እስራኤልን ነፃ አወጣቸው፡ እስራኤል ከግብፅ በወጡበት ወቅት ከብዛታቸው የተነሳ ግብፅ የተወረረች መንደር መሰለች፤ ባዶ ቀረች፤ በዚህ ጊዜ ፈርዖን ደነገጠና አግባ መልስ በማለት ፈረስ ሰረገላውን አስጭኖ ሠራዊቱን አስከትሎ እስራኤልን ከመንገድ ለመመለስ ተከተላቸው ፡ ከኋላ ደርሶ እንዳያጠቃቸው እግዚአብሔር ቀን በደመና ጋርዶ ሌሊት በእሳት ዓምድ እየመራቸው ባሕረ ኤርትራ ደረሱ፤ በዚህ ጊዜ እግዚአብሔር ባሕሩን በበትርህ ምታው ሲል ሙሴን አዘዘው፡ ባሕሩን በበትሩ ቢመታው ውሀው ለሁለት ተከፍሎ እንደግድግዳ ቆመ፡ እስራኤልም ባሕሩን በእግራቸው ተሻገሩ፤ እስራኤል ባሕሩን ተሻግረው እንደቆሙ የደመናው መጋረጃ ተወገደ፡ እስራኤልና ፈርዖን ፊት ለፊት ተያዩ፡ ፈርዖን ከነሠራዊቱ ባሕሩን አቋርጦ እስራኤልን ለመያዝ በፈረስ በሰረገላው እንደተጫነ ዘሎ ገባ፤ ግንባር ቀደም አዝማቹ ሳይሻገር የኋላው ደጀን ጨርሶ ሲገባ እግዚአብሔር እንደገና ባሕሩን በበትርህ ምታ ሲል ሙሴን አዘዘው፤ ሙሴ

ባሕሩን በበትሩ ቢመታው እንደግድግዳ ቆሞ የነበረው ውሀ እንደበርሲን ግንብ ተደረመሰ፣ ፈርዖንን ከነሠራዊቱ ማዕበል አጥለቀለቀው፡ እስራኤል 515 ዘመን በግብፃውያን ከተገዙ በኋላ ኃያሉ የእስራኤል አምላክ ግብፃውያንን በውሀ ደምስሶ እስራኤልን ነፃ አወጣቸው፡ በዚህ ጊዜ እስራኤል "እግዚአብሔርን እናመሰግነዋለን ፡ ፈርዖንን ከነሠራዊቱ ወደባሕር ጣለው" በማለት ነፃ አውጭውን አምላክ እግዚአብሔርን በከበሮ እያዘመሩ አመሰገኑት፡

እስራኤል ከግብፅ ከወጡ በኋላ እግዚአብሔር በሙሴ አማካይነት በምድረበዳ መና ከደመና አውርዶ ውሀ ከድንጋይ አፍልቆ 40 ዘመን መግቧቸዋል፡ እግዚአብሔር እስራኤልን ነፃ ካወጣቸው በኋላ እንዲሁ አልተዋቸውም ፤ ሙሴን ወደደብረሲና ጠርቶ ቃል በቃል እያነጋገረ ሕገ መንግሥቱን (አሰራሩን ትዕዛዝ) በፅላት ጽፎ ሰጥቶታል ።

ሙሴ በምድረበዳ እስራኤልን እየመራ ሲያስተዳድራቸው የሚበሉትና የሚጠጡት ሲጎድልባቸው በሙሴ ላይ ያጉረመርሙና ያበሳጩት ነበር፣ ከዕለታት አንድ ቀን በቃዴስ ምድረበዳ ውሀ ጠፍቶ ቢጮሁበት ወደ እግዚአብሔር አመለከተ፡ እግዚአብሔርም ሕዝቡን ሰብስብና በትርህን ወስደህ ድንጋዩን ምታው ፡ ውሀ ይወጣልሃል አለው። ሙሴና አሮንም ሕዝቡን ሰበሰቡና እናንተ አጉረምራሚዎች አሁን ከዚህ ውሃ እናወጣላችኋለን በማለት በበትሩ ድንጋዩን ቢመታው ቀዝቃዛ ውሀ ፈለቀላቸው፣ ጠጡ፣ በዚህ ጊዜ ሙሴና አሮን ዮርዳኖስን ሳይሻገሩ ምድረ ርስት ሳይደርሱ እንደሚሞቱ አስጠነቀቃቸው ፡ አሮን ሆር በሚባል ተራራ ሥር ሞቶ ተቀበረ፡ ሙሴ ግን ምድረ ርስትን አሻግሮ ያይ ዘንድ እግዚአብሔር ወደ ናባው ተራራ አወጣው፣ በኢያሪኮ ትይዩ ምድረ ርስትን ካሳየው በኋላ በወንዙ ዳር ቀበረው፡ መቃብሩ የት እንዳለ አይታወቅም፣ ሙሴ ሲሞት የ120 ዘመን ሰው ነበረ፡ ዘኁ 20 ቁ 10 ፡ ዘዳ 32 ቁ·49 ፤ 34ቁ 5፡

ደመና ጋርዶ ጠላት አሰጥሞ እስራኤልን ከግብፃውያን ባርነት ነፃ ያወጣው ታላቁ እስራኤላዊ ጀግና ሙሴ በክርክር ውሀ ምክንያት እተስፋይቱ አገር ምድረርስት ሳይደርስ እመንገድ ላይ ተቋርጦ መቅረቱ አስገራሚ ነው፡ ይህ አንጋፋ መሪ ሙሴ እንደሞተ ወጣቱ መስፍን ኢያሱ ወዲያው ምስፍናውን ተረክቦ እስራኤልን መምራት ጀመረ፡ ቀደም ሲል "ከወንድሞቻችሁ መካከል እንደኔ ያለ ነቢይ ያስነሳላችኋል" ሲል ሙሴ የተናገረው ትንቢት ደረሰ ተፈጸመ፣ ዘዳግም 18 ቁ· 18 ፤ ዮሐ 1ቁ 46፣ ኢያሱ ምስፍናውን ተረክቦ እስራኤልን እየመራ ወደ ተስፋይቱ አገር ጉዞ ሲጀመር የእግዚአብሔር የኪዳኑን ታቦት አሸክሞ ካህናቱን አስቀደመ፤ በዚህ ጊዜ የዮርዳኖስ ወንዝ እንደ ኤርትራ ባሕር ለሁለት ተከፍሎላቸው እስራኤል በአግራቸው ተሻግረዋል፤ ኢያሱ እስራኤልን እየመራ ዮርዳኖስን ከተሻገረ በኋላ በተስፋይቱ አገር በከነዓን የሚኖሩትን የአሕዛብ ነገሥታት በእጁ እንደሚጥልለት እግዚአብሔር ቃል ገባለት፡ አይዞህ አትፍራ አለው፤ ኢያሱም በተስፋይቱ ምድር በከነዐን ይኖሩ የነበሩትን ቁጥራቸው ከ30 በላይ የሆኑትን ነገሥታት አንድ ባንድ ደምስሶ ምድረ ርስትን በእጁ አስገባ፤ ከነዚህ ነገሥታት መካከል አንዱ የሆነው አምራዊ የተባለው ኃይለኛ ጠላት በጀግንነት እየተዋጋ ሳይሸነፍ ቀኑ ቢመሽበት ኢያሱ ዐሐይና ጨረቃን ባሉበት እንዲቆሙ አድርጓል፤

ኢያሱ ከሙሴ ባላነሰ ሁኔታ እስራኤልን እየመራ ባሕር ከፍሎ በታላቅ ጀግንነት የእስራኤልን ጠላቶች ደምስሶ ወደተስፋይቱ አገር ወደከነዐን ከገባ በኋላ ለያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ ምድረ ርስትን በገመድ እየሸነሸነ አካፍሏቸዋል፡ ኢያሱ ይህን ካደረገ በኋላ ዕድሜ ጠግቦ በ110 ዘመኑ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቷል፤ መጽሐፈ ኢያሱ 10 ቁ1—13 ፤ 12 ቁ1—24 ፤ 24 ቁ29።

ሙሴ ልዩ ባሕርይ ነበረው ፤ ሙሴ እንደበቱ ልቱት ከቡደ መዝራዕት ነበር ፡ አንደበቱ እንዴት ልቱት (ኮልታፋ) ሊሆን ቻለ ? ቢባል ወደኋላ ተመልሶ የእስራኤልን ታሪክ መዳበስ ያስፈልጋል ፤ እስራኤል በግብፅ ምድር 515 ዘመን ኖረዋል ፡ እስራኤል በግብፅ ያህን ያህል ዘመን ሲኖሩ ራሳቸውን ችለው መንግሥት መሥርተው አይደለም ፤ ድንጋይ እየፈለጡ ኖራ እየረገጡ ከዚህም ሌላ ለግብፃውያን የቤት አሽከሮች ሆነው ሲያገለግሉ ኖረዋል ፤

እስራኤል እንደዚህ ተረግጠው እየተገዙ ቁጥራቸው ከግብፃውያን እጥፍ እየጨመረ ያድር ነበር ፡ ከሚደርስባቸው ግፍና በደል የተነሳ ዓመፅ ቢቀሰቅሱ ግብፃውያንን ሊያጠቁ ይችላሉ የሚል ስጋት ስላደረባቸው ንጉሡ ፈርዖንና መኳንንቱ የእስራኤል ሴቶች ወንድ ሲወልዱ እያነቁ



www.ethiopianorthodox.org

የሚገድሉ አዋላጆች ሾሙባቸው ፤ በዚህ መሠረት ወንዶች ሲወለዱ እየታነቁ ይገደሉ ጀመር ፡ በዚህ ወቅት ነው ሙሴ የተወለደው ፡ ሙሴ መልከ መልካም ነበር ፡ አዋላጇቱ አይታ ይህንስ የፈጠረው ይግደለው በማለት አዝናለት ትታው ሄዳለች ፤ እናቱ በጥቆማ ያስገድሉብኛል ብላ ስለሰጋች ቅርጫት ሠርታ በዝፍት ለቅልቃ ዓባይ ወንዝ ዳር እፊላ ሥር ደብቃ አኖረችው ፤ አሞራ ዓይኑን እንዳይጠነቁለው እህቱ ማርያም በሩቅ ሆና በዓይን ቁራኛ ትጠብቀው ነበር ፤ እናቱም በተወሰነ ሰዓት እየሄደች ታጠባው ነበር ፤

ከዕለታት አንድ ቀን የንጉሡ የፈርዖን ሴት ልጅ ዓባይ ወንዝ ዳር ስትንሸራሸር ከሩቅ ቅርጫቱን አይታ ይህ ምንድነው ? በማለት ቅርጫቱን አስመጥታ ብታይ የወርቅ ፍልቃቂ የመሰለ ልጅ አገኘች ፤ የእስራኤል ሴቶች እንዳይገድሉባቸው ከዚህ ደብቀውት ነው ፤ ይህንስ ለንጉሡ ልጅ ወለድሁ ብዬ ነግሬ እኔ አሳድገዋለሁ በማለት ወደቤተ መንግሥት ስትወስደው በሩቅ ሆና ትመለከት የነበረችው እህቱ ማርያም ቀረብ አለችና በዚህ ሰሞን ልጇ የሞተባት ሴት አለች ፤ ላምጣልሽና እያጠባች ታሳድግልሽ አለቻት ፤ ልዕልቲቱም እሺ አምጪልኝ አለቻች ፡ እግዚአብሔር ባወቀ እናቱ ተጠርታ መጥታ ሞግዚት ሆነችው ፤ ሙሴም የንጉሡ የልጅ ልጅ እየተባለ በቤተ መንግሥት ተቀማጥሎ አደገ ፤ ዘፀ 2 ቁ 1–10 ፤

ንጉሡ ፈርዖን የልጅ ልጁን የሙሴን ሶስተኛ ዓመት የልደት በዓል ሲያከብር ለመኳንንቱና ለወዛዝርቱ ታላቅ ግብዣ አድርጎ ሳለ ንጉሡ የሕፃኑን ዓይን እየተመለከተ ሲደሰት ሕፃኑ ቀና ብሎ የንጉሡን ፊት በጥፊ አጮለው ፤ በዚህ ጊዜ ንጉሡ ጥፊው ስለተሰማው ተቆጣና ሕፃኑን ገፍትሮ ሊጥለው ሲዳዳው መኳንንቱ አይተው ይህ ሕፃን እኮ ነው ? ምን ያውቃል? በማለት ቁጣውን ካበረዱለት በኋላ ማወቅ ያለማወቁን ለመለየት ባንድ ሳህን ፍትፍት በሁለተኛው ሳህን ፍም እሳት አድርገው አቀረቡለት ፤ በዚህ ጊዜ ሕፃኑ ሙሴ እጁን ወደፍትፍቱ ሊዘረጋ ሲሞክር እግዚአብሔር እጁን ጠምዝዞ ወደ እሳቱ እንዲያመራ አደረገው ፤ ሙሴ እሳቱን አነሳና ቢጎርሰው ምላሱን ድብን አድርጎ ጠበሰው ፤ በዚህ ጊዜ ሙሴ ዋይ ብሎ ስለጮኸ ንጉሡን በጥፊ የመታው ባለማወቅ ነው ተባለለት ፡ ንጉሡም



ከቁጣው በረደ ፡ ከዚህ የተነሳ ሙሴ ሲናገር ምላሱ ኮልታፋ ሆኖ ቀረ ይባላል ፡ ይኸውም ይታወቅ ዘንድ እግዚአብሔር ሕዝቤን እስራኤልን ከግብፅ ነፃ አውጣልኝ ብሎ ቢያዘው አንደበት የለኝም "ሲል መልሶለታል፡ ዘፀ 4 ቁ 16 ተመልከት ፡

ለ/ ሙሴ ከቡደ መዛራዕት (ኃይለኛ) ነበር ፤ ሙሴ በጎልማሳነቱ ጊዜ አንድ እስራኤላዊ በበጠበጠው አንድ አንድ ግብፃው ገፍትሮ ጥሎ ልብሱን ሲያጥብበት አየ ፡ በወገኑ መጠቃት የተበሳጨው ሙሴ ግራና ቀኝ ተመልክቶ ባካባቢው ሰው እንደሌለ ካረጋገጠ በኋላ (ኃይለኛው ሙሴ) በክርን አንድ ጊዜ ቢያሳርፍበት ግብፃዊውን ሶስት ክንድ ያህል አሸዋ ውስጥ ቀብረው ፡ እንደዚሁም በሌላ ጊዜ ሁለት እስራኤላውያን ተጣልተው ሲጨቃጨቁ ሙሴ ደርሶ እናንተ ደግሞ ሁለታችሁ ወንድማማቾች ናችሁ ፤ ለምን ትጣላላችሁ ? በማለት አጥፊውን ቢገሥፀው አንተን በእኛ ላይ ፈራጅ አድርጎ የሾመህ ማነው ? ወይስ ትናንት ያን ግብፃዊ እንደገደልህ ዛሬ ደግሞ እኔን ልትገድለኝ ትፈልጋለህ ? ሲል ያደረበትን ስጋት ተናገረ ፡ በዚህ ጊዜ ሙሴ ቀደም ሲል የፈጸመው ድርጊት በሰው ዘንድ ይልቁንም በፈርዖን ዘንድ እንደታወቀበት ስለተረዳ ከግብፅ ምድር ወደምድያም ተሰደደ ፤ ዘፀ 2 ቁ 12–16 ፤

ሐ/ ሙሴ እንዴት ተቀበረ ? ሙሴ እስራኤልን ከግብፅ ነፃ አውጥቶ እየመራ ዮርዳኖስ ወንዝ ሲደርስ ቀደም ሲል በክርክር ውኃ ምክንያት ወደ ተስፋይቱ አገር አትገባም ሲል እግዚአብሔር ባስጠነቀቀው መሠረት ናበው ወደተባለው ተራራ አውጥቶ ምድረ ርስትን በሩቅ ካሳየው በኋላ በሞዓብ ሏጊድ በወንዝ እንደቀበረው ታሪኩ ያስረዳል ፤ ዘዳግም 34 ቁ5–6 እንዴት ተቀበረ ? ቢባል ሁለት መላእክት መቃብሩን ቆፍረው ወርዱም ሆነ ቁመቱ አንተን የሚያህል ሰው ስለሞተብን ከዚህ ገብተህ ለካልን አሉት ፡ ሙሴ ማለት የዋኅ ቅን ማለት ነው ፡ እሺ በማለት ገብቶ ጋደም ሲል ሁለቱ መላዕክት ከነሕይወቱ አፈር አለበሱት (ቀበሩት) ይባላል ።

እስከዚህ ድረስ የዘዳግምን 18 ቁ 18 ትንቢት መነሻና መድረሻ ለማስረዳት ረዥምም ጉዞ አብረን ተጉዘናል ፡ አሁን ደግሞ ቀደም ሲል እኔና ሽሁ ወደጀመርነው የሃይማኖት ጉባኤ /ክርክር/ እመልሳችኋለሁ ፤

www.ethiopianorthodox.org

# እስማኤል የበኩር ልጅ

"ካህኑ የምናገረውን እያንዳንዷን ነጥብ ሳያምኑታ በመስማማቱ ከወንድሞቻችሁ መካከል እንደአንተ ያለ ነቢይ አስነሳላችኋለሁ" ከሚለው ካንድ ሙሉ ትንቢት ውስጥ አንዷን ነጥብ ብቻ ነው ለማረጋገጥ የሞከርሁት ፤ ይኸውም "እንዳንተ ያለ" "አንተን የመሰለ" "ሙሴን የመሰለ" የሚለውን ሐረግ ማረጋገጥ ነው ፤ ከወንድሞቻችሁ መካከል ለሚለው ሐረግ አጽንኦት ሰጥተነዋል ፤ ከዚህ ላይ ሙሴና ሕዝቦቹ አይሁዳውያን እንዳንድ ነገድ ተለይተው ተጠርተዋል ፤ በዚህ መልኩ "ወንድሞቻችሁ" የሚለው ያለአንዳች ጥርጥር ዓረቦች ይሆናሉ ማለት ነው ፤ መጽሐፍ ቅዱስ አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ እንደሆነ ይናገራል ፤ አብርሃም ሁለት ሚስቶች ነበሩት ፤ ሣራና አጋር ፤ አጋር ለአብርሃም የበኩር ልጅ የሆነውን ወንድ ልጅ ወልዳለታለች ፡ "አብርሃም አጋር የወለደችለትን የልጇን ስም እስማኤል ብሎ ጠራው" ዘፍ 16 ቁ 15 ፤ ልጁ እስማኤል የቁልፈቱን ሥጋ በተገረዘ ጊዜ የ13 ዓመት ልጅ ነበር" ዘፍ 17 ቁ 25 ፤

"እግዚአብሔር ለአብርሃም እስከተገለጠበት ጊዜ ድረስ እስማኤል የአብርሃም ብቸኛ ልጅና ዘር ነበር ፤ እግዚአብሔር እንደገና ለአብርሃም በሣራ አማካይነት ይስሐቅ የሚባል ወንድ ልጅ ሰጠው፡ እርሱም የእስማኤል ታናሽ ነው፡ እስማኤልና ይስሐቅ ያንድ አባት የአብርሃም ልጆች ከሆኑ ወንድማማቾች ናቸው ማለት ነው ፤ እንዲሁም ያንዱ ልጆች ለሌላው ልጆች ወንድሞቻቸው ናቸው ፤ የይስሐቅ ልጆች አይሁዶች ሲሆኑ የእስማኤል ልጆች ደግሞ ዓረቦች ናቸው ፡ ስለዚህ ወንድማማቾች ናቸው ፡ በዚህ መሠረት ሙሐመድ ከእስራኤላውያን ወንድሞች መካከል የተነሱ ነቢይ ናቸው ፡ ምክንያቱም የአብርሃም ልጅ የሆነው የእስማኤል ዝርያ አካል ናቸውና ፡ "ከወንድሞቻችሁ መካከል" የሚለውም ትንቢት በትክክል ያስቀመጠው ይህንኑ ነው ፡ ሙሴን የሚመስለው የወደፊቱ ነቢይ የሚነሳው ከወንድሞቻችሁ መካከል እንጅ ከቶም ከእስራኤል ልጆች እንዳልሆነ ትንቢቱ በግልጥ ለይቶ ጠቅሶታል ፡ በዚህ መሠረት ከወንድሞቻችሁ መካከል የተነሱት ነቢይ ሙሐመድ መሆናቸው ግልጥ ነው" ሲል የመላምቱን ስልት እየቀያየረ የሚጓዘው ሸህ አህመድ አሁን ደግሞ የመጨረሻውን አዲስ መላምት እየሞከረ ነው ፤

በዘዳግም 18 ቁ·18 ትንቢት ላይ የተመሠረተው የፈጠራ መላምት ከክርስትናው ዓለም ብርቱ ተቃውሞ እንደሚገጥመው ሸህ አህመድ ከወዲሁ በሚገባ ስለሚያውቅ ቀደም ሲል የተነገረውን ትንቢት ከእስራኤል የሥጋ ዝምድና ጋር ለማስተሳሰር ስልቱን ቀይሮ የእስማኤልንና የይስሐቅን ጥንታዊ ዝምድና በሰፊው ዘርዝሯል፡ እስማኤልና ይስሐቅ የአንድ አባት የአብርሃም ልጆች መሆናቸውን የሚክድ የለም፡ ሁለቱ ወንድማማቾች ካንድ አባት ቢወለዱም ከተለያዩ ሴቶች መወለዳቸውን መርሳት የለብንም፡ አንደኛዋ ሕጋዊት ሚስት ሁለተኛዋ ገረድ ናቸው፡ እመቤቲቱ ሣራ ገረዲቱ አጋር ይባላሉ፡

አብርሃም የእግዚአብሔር ወዳጅ እንደመሆኑ መጠን ሁለቱም ሴቶች ለአብርሃም ልጆች ወለዱለት፡ እግዚአብሔር ባወቀ ለሁለቱም ልጆች የተለያየ ዕድልና በረከት ሰጣቸው፡ "እስማኤልን ታላቅ ነገድ አደርገዋለሁ ፡ አሥራሁለት አለቃ ይወልዳል ፡ ከይስሐቅ ጋር ግን ኪዳኔን አፀናሁ፡ ለዘላለም ከርሱም በኋላ ለዘሩ " ይላል ዘፍ· 16 ቁ·19

"ከይስሐቅ ጋር ኪዳኔን አጸናለሁ" የሚለው ኃይለ ቃል ተራ ነገር አይደለም፡ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን ነው፡ ይህ ቃል ኪዳን በሁለቱ ወንድማማቾች ማለት በእስማኤልና በይስሐቅ ልጆች መካከል የብረት አጥር ሆኖ ለይቷቸው ይኖራል፡ ይህን የብረት አጥር በኃይል ደርምሶ ከይስሐቅ ልጆች ከእስራኤል ጋር መቀላቀል አይቻልም፡ በስመ ተወላጅነት በረከታቸውንም ሆነ ሀብተ ትንቢታቸውን ለመጋራት መከጀል የሕልም እንጀራ ነው፡ "ኪዳኔን አጸናለሁ" የሚለውን ባጭሩ ለመተንተን ቢያስፈልግ አብርሃም ካገሩ ከካራን ሲወጣ እግዚአብሔር በገባለት ቃል ኪዳን መሠረት የተስፋይቱን ምድር ከነዓንን የሚወርሱ የይስሐቅ ልጆች እስራኤል በመሆናቸው ፡ አጋርና ሣራ በደብረሲናና በኢየሩሳሌም የተደነገጉት የሁለቱ ሕጎች (የኦሪትና የወንጌል) ምሳሌዎች መሆናቸው፡ እንደ ዳዊት እንደ ሰሎሞን እንደ ሙሴና እንደ ኢያሱ ያሉት ታላላቅ ነቢያትና መሪዎች (ነገሥታት) የሚነሱት ከእሥራኤል መካከል በመሆና



www.ethiopianorthodox.org

ቸው፡ በመጨረሻም ነቢያት ይውረዳል ይወለዳል ብለው ትንቢት የተናገሩለት መሢሕ ክርስቶስ የሚወለደው ከነዚሁ ከእስራኤል በመሆኑ ኪዳኔን ከይስሐቅ ጋር አጸናለሁ ብሏል፤ እንግዲህ እግዚአብሔር ያለምክንያት ከሰዎች ጋር ቃል ኪዳን አይገባም፤ የገባውንም ቃል ኪዳን አያጥፍም፡ እንኳን የእግዚአብሔር ቃል ኪዳን የሰው ልጅ ቃል ኪዳን ይከበራል፡ ይጠበቃል፤ አባቶቻችን“ የተናገሩት ከሚጠፋ የወለዱት ይጥፋ ይላሉ፡” እውነት አላቸው።

ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልዕክቱ “ተጽኗልና ለአብርሃም ሁለት ልጆች እንደነበሩት፤ አንዱ ከባሪያይቱ ሁለተኛው ከእመቤቲቱ የተወለዱ ፡ ነገር ግን የባሪያይቱ ልጅ እንደሥጋ ተወለደ፡ ከእመቤቱቱ የተወለደው ግን በተስፋ ነው ይላል…” ገላ· 4 ቁ· 22–25

ይሁን እንጂ ባሁኑ ጊዜ ለይስሐቅና ለዘሮቹ የተነገረው ትንቢትየተሰጠው ተስፋ እኛም ከአብርሃም ዘር የተወለደው የእስማኤል ዘሮች በመሆናችን ይገባናል ብለው እነአህመድ ዲዳት መጠየቃቸው እግዚአብሔርን የሚያሳዝንና የሚያስቆጣ የድፍረት ሙከራ ነው፡ ምክንያቱም የተስፋውን ቃል የሚሰጥና ትንቢት የሚያናግር እግዚአብሔር ነውና ከላይ ከእግዚአብሔር ያልተሰጠን ተስፋና ሀብተ ትንቢት ትውልድ ቆጥሮ ሐረግ መዝዞ የሚወርሱት ሀብት ርስት አይደለም፡ “አሁንም ለንስሐ የሚገባ ፍሬ አድርጉ፤ አብርሃም አባታችን ነው በማለት የምታመልጡ አይመስላችሁ፡…” ይላል ማቴ· 3 ቁ· 8።

እንኳን ከተለያዩ ሴቶች በተለያየ ጊዜ ለተወለዱ ልጆች አንድ ቀን ተዘርተው አንድ ቀን ለተወለዱ ልጆች እግዚአብሔር የሚሰጠው ዕድልና በረከት የተለያየ ነው፤ ለምሳሌ ኤሳውና ያዕቆብ ካንድ አባትና ካንዲት እናት የተወለዱ መንታ ወንድማማቾች ናቸው፤ ገና በእናታቸው ማሕፀን ሳሉ “ታላቁ ለታናሹ ይገዛል” ሲል እግዚአብሔር ባወቀ መጭውን ዕድላቸውን ተናገረ፤ ዘፍ· 25 ቁ· 23 ሮሜ·9 ቁ· 10፤ እንግዲህ እግዚአብሔር ይህን በማድረጉ ተሳስቷል እንላለን? አንልም፤ እንደዚሁም “ከወንድሞቻችሁ መካከል እንደ እኔ ያለ ነቢይ ያስነሳላችኋል” ተብሎ ለኢየሱስ ምሳሌ ሆኖ ትንቢት ለተነገረለት ከሙሴ ቀጥሎ የእስራኤል መስፍን ለሆነው ለኢያሱ የተሰጠው ሀብትና በረከት በስመ ተወላጅነት



ለእኛም ይገባል ተብሎ መነሳሳት ሰጭውን እግዚአብሔርን መፈታተን ነው፤ ክርስቶስ በቤተ መቅደስ ጉልላት ላይ ተቀምጦ ሰይጣን ባየው ጊዜ የእግዚአብሔር ልጅስ ከሆንህ ዘለህ ውረድ አለው፡ “ኢየሱስም እግዚአብሔር አምላክህን አትፈታተነው ተብሎ ተጽፎብሃል” ሲል መልሶለታል፤ ማቴ· 4 ቁ· 5–7 ዘዳግም 6 ቁ· 16፤

# አስፈሪ ማስጠንቀቂያ

“ታማኙ ምስክር” የማያነበው ነቢይ አልፎም የተአምራት ተአምር” ለተሰኙት ንዑሳን ክፍሎች መልስ ለመስጠት አልፈልግም፤ ምክንያቱም ምሥጢር ከሆነ ምሥጢር ነው፡ ተከድኖ ይብሰል፡ ተአምር ከሆነ ደግሞ እንደሙሴ እንደ ኢየሱስ ሕዝብ እያወቀው ፀሐይ እየሞቀው ባደባባይ መተግበር አለበት፤ እግዚአብሔር እንዲታወቅ የማይፈልገውን ምሥጢር ወደመሬት አያስተላልፍም፤ አንዲት ልጃገረድ (ድንግል ማርያም) በድንግልና ወንድ ልጅ እንድትወልድ ከማድረግ የበለጠ ምሥጢር የለም፤ ይህን አስደናቂ ምሥጢር እግዚአብሔር በድብቅ አልፈጸመውም፤ በኢየሩሳሌም አውራጃ ሕዝብና አሕዛብ በተሰበሰቡበት አደባባይ በቤተልሔም ዓለም እንዲያውቀው ፀሐይ እንዲሞቀው አድርጓል፤ ሉቃ፡ 2 ቁ·1–7፤

“አስፈሪ ማስጠንቀቂያ” ለሚለው ንዑስ ክፍል ግን አጭር ማብራሪያ ልስጥበት እወዳለሁ፡ አዲስ በፈጠረው ተልካሻ መላምት የፈነደቀውና እጅግ የተኩራራው ሸህ አህመድ ዲዳት ትንቢቶች በልክ እንደተሠራ የእጅ ጓንት ከሙሐመድ ጋር እንዴት እንደተጣጣሙ ተመልክት፤ ትንቢቶች በሙሐመድ መፈጸማቸውን ለማረጋገጥ ትንቢቶችን መለጠጥ አያስፈልግም በማለት እንዳለፈው ሁሉ ከቂሱ የአዎንታ መልስ እየጠበቀ አስተያየቱን አቀረበለት፡ እስካሁን ምንም ዓይነት ተቃውሞ ሳያሰማ በለዘብተኝነት የቆየው ቂስም በዚህ ጊዜ ስሜቱ ገንፍሎ የቀረቡት ነጥቦች በሙሉ ምክንያታዊነትን የተላበሱ ቢመስሉም አንዳችም የሚፈይዱት ተጨባጭ ውጤት የላቸውም፡ ምክንያቱም እኛ ክርስቲያኖች በሥጋ ተገልጦ ከኃጢአት መቀመቅ አርነት ያወጣንን ሕያው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስን እናምናለን በማለት ሸህ አህመድ ሲልበው ሲከበው የከረመውን የፈጠራ መላምት ባዶ ዓረፍተ ነገር የልጆች ጨዋታ (የእንቧይ ካብ) አደረገበት፤ (ናደበት) ተገቢ መልስ ነው፤ ዛሬም እኛ ክርስቲያኖች

www.ethiopianorthodox.org

የቄሱን ቃል በመድገም "ኢየሱስ (ወልድ) የሌለው ማለት የክርስቶስን አምላክነት ያልተቀበለ ወገን ሕይወት የለችውም" በማለት ለጽሑፉ አዘጋጅና ለመሰሎቹ እናረጋግጥላቸዋለን፡ 1 ዮሐ· 5 ቁ· 12፤ ሸህ አህመድ ትንቢቶችን መለጠጥ አያስፈልግም ብሎ ነበር፤ ይሁን እንጂ ራሱ ትንቢቶችን ለመለጠጥ ሞክሮ ከሙሐመድ ዘንድ ሳይደርሱ ከጥቅም ውጭ ሆነው ቀርተዋል፤ ሸህ አህመድ እስካሁን እንደፈለገው ያቀረበለትን ጥያቄ ሁሉ ያለምንም ተቃውሞ በትዕግሥት ይከታተል ከነበረው ቄስ ያልጠበቀው ከረር ያለ መልስ በማግኘቱ በቀቢፀ ተስፋ ታዲያ! አያስፈልጉም? ችላ ልበላቸው እንዴ? ሲል ጠየቀው፤ ቄሱም ቀበል አደረገና መቸም አመልክ እንዲህ አይልም፡ የማስጠንቀቂያ ቃሉን ይከትቡለት ዘንድ መሻቱ ከቶ ለዋዛ አይደለም፡ ለቃሉ ሊቸር የሚገባውን ክብር የሚነፍጉና ቸልታን የሚያደርጉ እንዳንተ ያሉ ሰዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ አስቀድሞ ስለሚያውቅ ከኦሪት ዘዳግም ምዕ· 18 ቁ· 18 ጋር ከረር ያለ ማስጠንቀቂያውን ያስከተለው ለዚህ ነው ይልና ማስጠንቀቂያውም" በስሜ የሚናገረውን ቃሌን የማይሰማውን ሰው እኔ እበቀልለታለሁ ይላል፤

ይህ ማስጠንቂያያ አያሸብርህም? አንዳች የማይሳነው ኃያል ፈጣሪ በቀልን እየዛተ እኮ ነው… አንተ ግን ለኃያሉ ፈጣሪ ማስጠንቀቂያ ቅንጣት ታህል ፍራቻ የለህም ሲል አስገንዝቦታል፤ ይሁን እንጂ ሸህ አህመድ ማስጠንቀቂያውንም ሆነ ማስገንዘቢያውን ከግምት ውስጥ አላስገባውም፡ እንግዲህ የሸህ አህመድ ዕጣ በዘዳግም 18 ቁ· 20 ላይ " ነገር ግን ይናገር ዘንድ ያላዘዝሁትን በስሜ በድፍረት የሚናገር ወይም በሌላ አማልክት ስም የሚናገር ነቢይ ርሱ ይገደል" ስለሚል እንዲናገር ከእግዚሐብሔር ያልታዘዘውን ቃል በድፍረት ለሙሐመድ በመስጠቱ ፍርዱን ከእግዚአብሔር ይቀበላል፤ ራሱ እግዚአብሔር እኔ እበቀለዋለሁ ብሏልና፤ በዚህ ላይ እግዚአብሔር ሰዎችን የሚያነሳሳቸው ለበጐ ዓላማና ለሰው ልጆች ደህንነት ለእግዚአብሔር ንጹህ አምልኮት እንጂ እንደ ሸህ አህመድ ለአፍራሽ ተልዕኮ (ለተቃራኒው) አይደለም፤ በዚህ አንፃር በተቃራኒው መናፍቃንንና የዓመጽ መሪዎችን የሚያነሳሳቸው ሰይጣን ብቻ ነው፤ "የእግዚአብሔር ልጆችና የሰይጣን ልጆች በዚህ ይታወቃሉ፣ ጽድቅን (እውነትን) የማያደርግ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም፡… " ዮሐ·· 3 ቁ·10፡



# ሦስት መጠይቆች

አይሁድ "እንዳንተ ያለ ነቢይ አስነሳላችኋለሁ" ተብሎ በብሉይ ኪዳን የተነገረው ትንቢት ይፈጸም ዘንድ ይጠብቁ እንደነበረ ይታወቃል፤ በዚህ ወቅት ኢየሱስ የአይሁድ መሢሕ እኔ ነኝ ብሎ በመናገሩ በአይሁድ መካከል መከፋፈል ተፈጠረ፡ ግማሾቹ በተነገረው ትንቢት መሠረት የመጣ መሢሕ ክርስቶስ መሆኑን ለመቀበል የተዘጋጁ ሲሆኑ የቀሩት ደግሞ ኤልያስ ለሁለተኛው ጊዜ ይመጣል ብለው ተስፋ የሚያደርጉ ነበሩ፣ በሦሥተኛ ደረጃ መጥምቁ ዮሐንስ "መንግሥተ ሰማያት ቀርባለችና ንሥሐ ግቡ" በማለት እያስተማረ ሲያጠምቅ አይተው ግራ የተጋቡት አይሁድ ከኢየሩሳሌም ወደ ዮሐንስ መልክተኞችን ልከው አንተ ማነህ? ክርስቶስ ነህን? ኤልያስ ነህን? ነቢይ ነህን? ብለው ቢጠይቁት እርሱ ግን ሁሉንም አይደለሁም ሲል መለሰላቸው፤ እንግዲያውስ አንተ ራስህን ማነኝ ትላለህ? ቢሉት እኔ በምድረ በዳ የምጮህ ዓዋጅ ነጋሪ ነኝ፡ ኢሳይያስ የእግዚአብሔርን መንገድ አቅኑ፡ ጥርጊያውንም አስተካክሉ ብሎ እንደተናገረ አላቸው፡ ታዲያ አንተ ክርስቶስ ወይም ኤልያስ ወይም ነቢይ ያይደለህ ስለምን ታጠምቃለህ? ቢሉት እኔ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፣ በመካከላችሁ ግን የማታውቁት ቆሟል፡ እርሱ ነው በኋላዬ የሚመጣው እርሱም በፊቴ ነው፡ እኔ የጫማውን ማሠሪያ እፈታ ዘንድ የማይቻለኝ አላቸው፡ ዮሐንስ ከእኔ በፊት ከእኔም በኋላ ነው ማለቱ ክርስቶስ ጥንት የነበረ ዛሬም ያለ ወደፊትም የሚኖር የባሕርይ አምላክ መሆኑን ሲያረጋግጥ ነው፤ ዮሐ· 1 ቁ· 19·27 ኢሳ· 40 ቁ· 3፡

"ደቀመዛሙርቱ ኤልያስ አስቀድሞ ይመጣ ዘንድ ይገባዋል እያሉ ፈሪሳውያን ሲናገሩ ሰምተው ይህ እንዴት ነው? ሲሉ ኢየሱስን ጠየቁት፤ ኢየሱስም ኤልያበ አስቀድሞ ይመጣል ሁሉን ያቀና ዘንድ ካለ በኋላ "ኤልያስማ ፈጽሞ መጥቶ ነበር፡ የወደዱትን ሁሉ አደረጉበት እንጂ አላወቁትም አላቸው፤ በዚህ ጊዜ ኢየሱስ ኤልያስ እያለ በምሳሌ የሚናገረው መጥመቁ ዮሐንስን እንደነበረ ደቀመዛሙርቱ አስተዋሉ፤ ማቴ·17 ቁ· 11–13፡

ኢየሱስም ዮሐንስን ኤልያስ እያለ በምሳሌ መናገሩ አንዱን ለሌላው ተፃራሪ (ተቃዋሚ) አስመስሎ በማቅረብ ከሁለቱ አንዳቸው ያለጥርጥር

www.ethiopianorthodox.org

እውነቱን ከደዋል በማለት በሁለቱ መካከል መካካድ እንዳለ አድርጎ አቅርቦታል፡ ከሐዲ የሚባል ፍጡርን ከፈጣሪ ጋር እያነፃፀረ እውነቱን ከሐሰት ጋር እየቀላቀለ ፓንፍሌት በመርጨት ክዶ ለማስካድ ታጥቆ የተነሳው የጽሑፉ አቅራቢ ነው፡ ክርስቶስ ራሱን አይክድም፡ የምታደርጉትን አታውቁትምና መሐሪው አምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ ይቅር ይበላችሁ።

መጥምቁ ዮሐንስ "አንተ ክርስቶስ ነህን?" ተብሎ ለቀረበለት ጥያቄ ሲመልስ "እኔ ክርስቶስ አይደለሁም" ካለ በኋላ "እኔ የጫማውን ማሠሪያ እፈታ ዘንድ የማይቻለኝ ለመሢሕ ክርስቶስ ዓዋጅ ነጋሪ መንገድ ጠራጊ ነኝ ሲል ተልዕኮውን በሚገባ አስረድቷል፡ በዚህ ላይ መጥምቁ ዮሐንስ ስለትሕትና ነቢይ አይደለሁም ቢል ነቢይነቱን መካዱ አይደለም፡ ዮሐንስ ነቢይም ሰማዕትም ነው፡ ከዚህ ውጭ ያልሆነውን እኔ እንዲህ ነኝ ብሎ መዋሸት ነበረበት? ኢየሱስም ኤልያስ እያለ በምሳሌ የሚጠራው መጥምቁ ዮሐንስ መሆኑን በግልጽ ተናግሯል፡ ከዚህ ውጭ በሁለቱ መካከል ምን የተደበቀ ምሥጢር ነበረና ነው? በሁለቱ መካከል ቅራኔ ያለ አስመስሎ ማውራቱ፡ "ምናልባት የክርስትና ሃይማኖት ምሁራን ከሦስቱ ጥያቄዎች ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ እንጂ ሦስተኛው አያስጨንቃቸውም ይሆናል፡ እኛ ሙስሊሞች ግን ሦስተኛውና የመጨረሻው ጥያቄ ማለት "ነቢዩ ነህን?" የሚለው በእጅጉ ነው የሚማርከን "ካለ በኋላ በዘዳግም 18 ቁ· 18 ላይ ተመስርቶ ያን የተለመደውን "የሞኝ ልቅሶ መልሶ መልሶ" የተባለውን ዓይነት ጥቅስ በማንፀባረቅ "እንዳንተ ያለ ነቢይ" "እንደሙሴ ያለ ነቢይ" ተብሎ የተተነበየለት ሰው ሙሐመድ እንጂ ከቶ ኢየሱስ እንዳልሆነ ቀደም ብለን በበቂ ማስረጃዎች አረጋግጠናል" ብሏል፡ ሸህ አህመድ እኔም ቀደም ሲል በጭፍንና በድፍረት የቀረበውን የፈጠራ መላመት በብዕር ጫፍ ነካክቼ የልጆች ጨዋታ (የዕንቧይ ካብ) ያደረግሁት ስለሆነ አልመለስበትም፤ ሸህ አህመድ መጽሐፍ ቅዱስን የውሸቱ ማጣፈጫ የጽሑፉ ማስጌጫ አድርጎ ይቀልድበታል፤ ለዮሐንስ የቀረበለት ጥያቄ "ነቢይ ነህን?" የሚል ሆኖ ሳለ ሳድሱን ፊደል ወደ ካዕብ ለውጦ "ነቢዩ" ብሎ አንብቦታል፡ ነቢዩ ማለቱ መሐመድን ለማንፀባረቅ ነው፡ ዮሐንስ ነቢይ አይደለሁም ካለ በሞቱ ከዳ ቦታው ለሙሐመድ ይገባል የሚል አቋምም አለው፤ ሙሐመድን የሥልጣን ርካብ ለማቆናጠጥ የተደረገ ውጣ ውረድ ነው፤ "ወዳጆች ሆይ!



መንፈስን ሁሉ አትመኑ፡ ነገር ግን መናፍስቱ ከእግዚአብሔር እንደሆኑ መርምሩ፡ ብዙ የሐሰት ነቢያት ወደዚህ ዓለም መጥተዋልና፡" 1ኛ ዮሐ 4 ቁ· 1–2፡

## ሁሉን መርምሩ

ሸሁ ለክርስቶስ በጎች የምመክራቸው አለኝ ካለ በኋላ ማንም ነቢይ ነኝ ብሎ በመጣባችሁ ጊዜ ትጠነቀቁና ትመዝኑም ዘንድ እንድትጠቀሙበት ፈልጎ (መምህሩ) ራሱ የነገራችሁን ያን ብርቱ ሙከራ ለምን ሥራ ላይ አታውሉትም? እንዲህ ብሎ ስለነበር፡ "ከፍሬያቸው ታውቃቸዋለችሁ፣ ከእሾህ ወይን ከኩርንችት በለስ ይለቀማልን? እንዲሁ መልካም ዛፍ ሁሉ መልካም ፍሬን ያፈራል፡ ክፉ ዛፍም ክፉ ፍሬን ያፈራል፡… ከፍሬያቸው ታውቋቸዋለችሁ" ማቴ· 7 ቁ· 16–20፡

ለምንድን ነው ይህን ሙከራ በሙሐመድ ትምህርቶች ላይ ለመጠቀም የምትፈሩት? ካለ በኋላ ከፈጣሪ በተወረደው የመጨረሻ ቃል ኪዳን ቅዱስ ቁርዓን ውስጥ ዓለም በእጅጉ የሚናፍቃቸውንና ሰላምና ደስታ የሚያስፍኑትን የሙሴና የኢየሱስን ትምህርቶች ትክክለኛ ፍጻሜ ታገኙታላችሁ" ብሏል፡

"ራሷ ክርስትና ሳትነሳ ልታቋቁም ሄደች" ይባላል ፡ ሸህ አህመድ መጀመሪያ ራስህን አድን፡ ከዚያ በኋላ ለክርስቶስ በጎች መምህር ትሆናለህ፡ ላስተምራችሁ ትላቸዋለህ፡"አንተ ሆይ ሌላውን የምታስተምር በውኑ ራስህን አታስተምርምን? አስትረቁ ትላለህ አንተ ትሰርቃለህ፡" ሮሜ 2 ቁ· 21፡

መምህራችን ኢየሱስ ክርስቶስማ እንደ ሸህ አህመድ ያሉ የለየላቸው መናፍቃን የሐሰት ነቢያት እንደሚነሱ አስቀድሞ አውቆ " የበግ ለምድ ለብሰው ከሚመጡ ተኩላዎች ተጠንቀቁ" "በኋላ ዘመን ብዙ የሐሰት ነቢያት ይነሳሉ፡ ብዙዎችንም ያስታሉ"

"በፍሬያቸው ታውቋቸዋለችሁ፡ ከእሾህ ወይን ከኩርንችት በለስ አይለቀምም" "ከፈሪሳውያን እርሾ ተጠበቁ" … በማለት የመሳሰሉትን ማስጥንቀቂያዎች ለምዕመናን በጎቹ አስተላልፏል፡ በጎቹም ሌላ ጠቋሚና ተርጓሚ ሳያስፈልጋቸው ማስጠንቀቂያውን ነቅተው ተግተው ይጠብቁታል፤ ያም ሆኖ መናፍቃን አይተኙም።

www.ethiopianorthodox.org

እንደሸህ አህመድ ያሉት በክሕደት የተራቀቁት የዘመኑ መናፍቃን ስልታቸውን በመለዋወጥ የበግ ልምድ ለብሰው መጽሐፍ ቅዱስን እየጠቀሱ መፈታተናቸውን በሰፊው ቀጥለዋል፤ ነገር ግን አይሆንላቸውም፤ ትግላቸው ከግለሰቦች ጋር ሳይሆን ሰማይና ምድርን ከፈጠረው በኋላ ዘመንም ሥጋ ለብሶ ለሰው ልጆች ቤዛ ለመሆን በመስቀል ላይ ከሞተውና ሕያው ሆኖ ከተነሳው ከባሕርይ አምላክ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ነው፤ የበጎች እረኛ ኢየሱስ ክርስቶስም "እነሆ እኔ በዘመኑ ሁሉ እስከዓለም ፍጻሜ ድረስ ከእናንተ ጋራ ነኝ ሲል ቃል ኪዳኑን ትቶላቸዋል፤ ማቴ· 28 ቁ20፤

መጽሐፍ ቅዱስን ከዳር እስከዳር የዳሰሰው (ያነበበው) ሸህ በሙስሊሙ ሕብረተሰብ ዘንድ የሃይማኖት ነፃነት ያለ ለማስመሰል "ሁሉን መርምሩ" ሲል ከቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት የኮረጀውን ቀንጭቦ ጽፎታል፤ ሁሉን መርምሩ ማለት የተሻለውን ያዙ ለማለት ነው፤ ቀደም ሲል በትምህርቱ የዓለም ብርሃን የተሰኘው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ "ትንቢትን አትናቁ ፡ ሁሉን መርምሩ ፡ የተሻለውን ያዙ" ሲል የዓለም ኅብረተሰብ በዘር በሃይማኖት በፖለቲካና በማናቸውም የማኅበራዊ ኑሮ ዘርፍ የወደደውን ነፃ አቋም ተከትሎ ሕልውናውን እንዲመራ የሰጠው የመንፈስና የሞራል ነፃነት ነው፤ ተሰሎንቄ 5ቁ 20—21፤

## የመጽሐፉ ባለቤቶች

"በቅዱስ ቁርዓን ውስጥ ለአይሁድና ለክርስቲያኖች የተሰጠ የአክብሮት መአርግ ነው፡ በዚህ አንቀጽ ሙስሊም የሆነ ሰው" የመጽሐፉ ባለቤቶች ሆይ!" እናንተ የተማራችሁ ሰዎች ሆይ! እናንተ በመለኮታዊ ራዕይ የተወረደ ቅዱስ መጽሐፍ ተቀባይ ነን የምትሉ ሰዎች ሆይ! በእኛና በእናንተ መካከል የጋራ ወደሆነው ትክክለኛ ቃል "አላህን እንጂ ሌላን ላንገዛ" አንድ ላይ እንሰብስብ በማለት ወደቀጥተኛው ጎዳና እንዲጋብዝ ታዟል"፡ ይህም "በሚጠሉኝ እስከሦስትና አራት ትውልድ ድረስ የአባቶችን ኃጢአት በልጆች ላይ የማመጣ፣ ለሚወዱኝ ትዕዛዜንም ለሚጠብቁ እስከ ሺህ ትውልድ ድረስ ምሕረትን የማደርግ እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ቀናተኛ አምላክ ነኝና" የሚለውን ዘፀዓት 20 ቁ·5—6 ከጠቀሰ በኋላ "አይሁድና ክርስቲያኖች በዚህ የቁርዓን አንቀጽ ላይ ተካተው የቀረቡትን ሶስት ነጥቦች በመሠረታዊ ሐሳባቸው ይቀበሏቸዋል፡ በተግባር ግን አያውሏቸውም፤ ትምህርታቸው ካንድ እውነተኛ አምላክ ዋሕድና (አንድነት) ከመዘንበሉም በላይ የቅስና መዓረግም ጥያቄ ውስጥ የሚገባ ጉዳይ ነው፡ በአይሁድ ዘንድ እንዲያውም ቅስና በዘር የሚወረስ ነው፤ አንድ ፍጹም ሰብዓዊ የሆነ ፍጡር የእውቀቱ ልክ ያሊያም አጠቃላይ ንጽሕናው ከግምት ውስጥ ሳይገባ ካህን ወይም ጳጳስ ወይም ቄስ በመሆኑ ብቻ ራሱን ከፍ አድርጎ ይመለከታል፡ ወይም በሰውና በአምላክ መካከል እንደአገናኝ ሆኖ የሚያገለግል አድርጎ ራሱን ያስባል፡ በኢስላም ግን ቅስና የሚባል ነገር ፈጽሞ ቦታ የለውም" ተብሏል።

"ለሚወዱኝ ትእዛዜንም ለሚጠብቁ እስከሺህ ትውልድ ምህረትን የማድረግ" የሚል ተስፋው አጥንትን የሚያለመልም ማራኪ ቃል ኪዳን የሚገኘው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንጂ በቁርአን አይደለም፤ ቃል ኪዳኑም የተሰጠ ለመጽሐፉ ሰዎች (ለአይሁዶችና ክርስቲያኖች) እንጂ ለሙስሊሞች አይደልም፤ "የእንግዳ አፎሌ ባለቤቱን ያጎርሳል" እንደሚባለው ሸህ አህመድ የራሳችንን መንፈሳዊ ምግብ (መጽሐፍ ቅዱስን) እየጠቀለለ ሊያጎርሰን ሲሞክር ይታያል ፡ ከሰው ልጆች መካከል እግዚአብሔር የመረጣቸው ፡ ከሁሉ በፊት አምልካቱን የገለጠላቸው ቃል በቃል እያነጋገረ ሕጉን ትእዛዙን ፡ የሰጣቸው አምላካቸውን የሚወዱና የሚያከብሩ አምላካቸውም የሚወዳቸው እስከሺህ ትውልድ ምሕረቱን ቸርነቱን የሚለግሳቸው ለምርጥ ቤተሰቦች አይሁዶችና ክርስቲያኖች ነው፡

"የጋራ በሆነው ትክክለኛ ቃል አላህን እንጂ ሌላን ላንገዛ አንድ ላይ እንሰብሰብ" ብሏል ፡ ይህማ እንዳይሆን ከጊዜ በኋላ በእኛና በእናንተ መካከል እንጠረጠስ የተባለ ጨለማ የሰፈነበት ሰው ሠራሽ ገደል ተምሶ እኛ ወደ እናንተ እንዳንመጣ እናንተም ወደ እኛ እንዳትመጡ አግዶናል፤ አብርሃምና ባለፀጋው ነዌ ማዶ ለማዶ እየተያዩ ተነጋግረው ቀሩ እንጂ ሊገናኙ እንዳልቻሉ እኛና ሙስሊሞችም ፊት ለፊት እየተያየን የቃላት እንካ ስላንቲያ ከምንለዋወጥ በስተቀር በራሳችን ፍላጎት ያለ ክርስቶስ ፈቃድ ወደ ትክክለኛው የአምልኮት በረት እንሰበሰባለን ብሎ መገመት አስቸጋሪ ነው፤ ይሁን እንጂ ተአምረኛውና የተናገረውን የማያስቀረው የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ "ሌሎች በጎች አሉኝ፤ ከዚህ መንጋ


www.ethiopianorthodox.org

ያይደሉ፡ አመጣቸው ዘንድ ጊዜ አለኝ፣ ቃሌንም ይሰሙኛል፡ በጎችም ላንድ እረኛ አንድ መንጋ ይሆናሉ" ሲል የሰጠውን የትንቢት ቀጠሮ ተግባራዊ የሚያደርግበት ወቅት ሩቅ እንደማይሆን እኛና የሙስሊሙ ኅበረተሰብ በንቃትና በናፍቆት እንጠባበቃለን፤ ዮሐ· 10 ቁ·16፣

ሸህ አህመድ "ቅስና በአይሁድ ዘንድ በዘር የሚወረስ ነው በማለት ካጥላላ በኋላ በእስላም ግን ቅስና የሚባል ነገር ፈጽሞ ቦታ የለውም ብሏል፣ በሙስሊሙ ህብረተሰብ ዘንድ ቦታ የሌለው ቅስና ብቻ አይደለም፣ ምንም ነገር የለም፡ እግዚአብሔር በሥነ ሥርዓት እንዲመሰገንና እንዲገለገል ፈቃዱ ስለሆነ ወጉንና ሥርዓቱን ለመጽሐፉ ሰዎች (አይሁድና ክርስቲያኖች) ገልጦ አስተምሯቸዋል፡ አይሁድ በምኩራባቸው፣ ክርስቲያኖች በቤተ ክርስቲያናቸው እግዚአብሔርን እንዲያመሰግኑበትና እንዲያገለግሉበት የተሰጣቸው ወግና ሥርዓት ሰው ሰራሽ አይደለም፡ በሕግ መጽሐፍ (ብሉይ ኪዳን) ተደንግጎ ይገኛል፡

"እግዚአብሔርም ከሙሴ ጋር የተናገረውን ነገር በፈጸመ ጊዜ በደብረ ሲና ሁለቱንየምስክር ገበቶች ሰጠው፡ የድንጋይ ገበቶች በእግዚአብሔር ጣት የተጻፈባቸው ነበሩ"፡ "ሙሴም ተመልሶ ከተራራ ወረደ፡ ሁለቱም የምስክር ገበቶች በእጁ ነበሩ፡ ገበቶችም በሁለት ወገን የተጻፈባቸው ነበሩ፡ በግራና በቀኝ የተጻፈባቸው፡ ገበቶች የእግዚአብሔር ሥራ ነበሩ፡ የእግዚአብሔርም ጽሕፈት ተቀርፆባቸው ነበር" ዘፀዓት 31 ቁ·10፡ 32 ቁ 15 16 ተመልከት፡

"ከሰማያዊ ከቀይ ከቅርዝምዝም ግምጃ የሹመቱን ልብስ አደረጉ፡ በመቅደስ ለማገልገል የተቀደሰውንም የአሮንን ልብስ ሠሩ፡ እግዚአብሔር ሙሴን እንዳዘዘው"፡

"እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፡ በመጀመሪያው ወር ከወሩም በአራተኛው ቀን ማደሪያውን የማኅበሩን ድንኳን ትከል፡ የምስክሩንም ታቦት ከዚያ አኑር፡ በመጋረጃም ታቦቱን ጋርድ፡…" ዘፀ· 39 ቁ·1—5 ተመልከት፡

በብሉይ ኪዳን ቅስና (ክህነት) እግዚአብሔር ለፈቀዳላቸው ሰዎች ውርስ ነው፡ "አንተም አሮንን ወንድምህን ልጆቹንም ከእስራኤል ልጆች መካከል ለይተህ ወደአንተ አቅርብ፡ ካህናት ይሆኑልኝ ዘንድ አሮንን ናደብን አቢሁንአልዓዛርን ኢታምርን ልጆቹን፤ የመቅደስንም ልብስ



ለአሮን ለወንድምህ ትሠራለህ፡ ለክብርና ለጌጥ፡…የሻሽም ቀሚስ ሥራ፡ የሻሽም መጠምጠሚያ የተጠላለፈም መታጠቂያ፡ ለአሮን ልጆችም ቀሚስ አድርግ፡ ቀናትም ቆብም ለክብርና ለጌጥ፡ ይህን ሁሉ አሮንን ወንድምህን አልብሰው፡ ልጆቹንም ከርሱ ጋር፡ ቅባቸውም፡ እጃቸውንም ሙላቸው ቀድሳቸውም ፡ ካህናት ይሆኑልኝ ዘንድ"፡ ዘፀ· 28 ቁ·1—2 …ቁ·39—41 ተመልከት

በሐዲስ ኪዳን ደግሞ "እግዚአብሔር በቤተ ክርስቲያን ሰዎችን ሠራ፡ አስቀድሞ ነቢያትን ቀጥሎ ሐዋርያትን ሶስተኛ መምህራንን ከርሳቸው በኋላ ተአምራት የሚያደርጉትን ደግሞም ድውይ የሚፈውሱትን ልዩ ልዩ ቋንቋ የሚያውቁትን" 1ቆሮ 11ቁ 28፡ ኤፌ· 4 ቁ·11፡

"ማንም ከእናንተ ቢታመም የቤተ ክርስቲያንን ቀሳውስት ይጥራ፡ ይጸልዩለት፡ ዘይትም ይቀቡት በጌታ ስም፡ የሃይማኖት ጸሎት ድውዩን ይፈውሳልና፡ ኃጢአትም ቢኖርበት ይሰረይለታል"፤ ያዕ· 5ቁ·14—16፡

## ይድረስ ለሙሲሉሙ አፈቀላጤዎች

ይህን ዓለም በልዩ ልዩ ዕዕዋት እንስሳትና ዓራዊት አስጊጦ ፈጥሮ ለሰው ልጆች የሰጠ አምላክ በምድር ላይ ሊታወቅና ሊመሰገን ስለፈለገ አምልኮቱ የሚገለጥበትንና ስሙ የሚመሰገንበትን ስፍራ ለመምረጥ ነቢያትን አስነሳ፤ ትንቢት አናገረ፤ ሱባዔ አስቆጠረ፤ ከቦታ የተስፋይቱን ምድር ኢየሩሳሌምን ፡ ከነገድ እስራኤልን መረጠ፤ ከጊዜ በኋላ ደግሞ ባጭር ቁመት በጠባብ ደረት ተወስኖ ከአራቱ የዓለም መዓዝን ከሕዝብ ከአሕዛብና ከነገድ ሁሉ ክርስቲያኖችን ጠራ፡ ቤተ ክርስቲያንን ሠራ፡ ከመካከላቸውም አገልጋይ ካህናትን አዘጋጀ፡ "በምድር ያሰራችሁት በሰማይ የታሰረ ይሁን፡ በምድር የፈታችሁት በሰማይ የተፈታ ይሁን" ሲል ሥልጣን ሰጣቸው ፡ ማቴ·18 ቁ·18፡ የቤተ ክርስቲያን መገልገያ መሣሪያውን ነዋየ ቅድሳቱን ፈቀደ፡ መዝሙርና ከበሮውን ጸናጽልና መቋሚያውን ማለት ነው፡ መዝ· 150 ቁ· 1–6፤ ይህ ሁሉ በተጨባጭ ማስረጃ የተደገፈ ነው፡ ማስረጃውንም አንድ ባንድ ታውቂታላችሁ፤ ታዲያ ለምን የእግዚአብሔርን ችሮታ ትቀናቀናላችሁ? ለምንስ በክርስትና ሕይወት ላይ መሰቃ ትናገራላችሁ? ሕሊናችሁ አይወቅሳችሁምን? በዚህ ላይ እግዚአብሔር በቸርነቱ ለወደደውና ለመረጠው ምድራዊ ሀብቱንና ሰማያዊ በረከቱን ቢሰጥ ለምን ዓይናችሁ ደም ይለብሳል? የእግዚአብሔር

www.ethiopianorthodox.org

መንግስት እኮ በቅናት አይወረስም፤ ይህ በእግዚአብሄር ቸርነት ላይ በድፍረት ብቻ የምትነዙት ፕሮፓጋንዳ በመጨረሻይቱ ቀን እንደሚያስፈርድባቸው አትጠራጠሩ፣ "የሙስሊሙ አቋም ግልጥ ነው፣ ሙስሊሙ በተለይ የራሴ ነው ብሎ ያዋቀረው ሀይማኖት እንዳለ አድርጎ አያወራም፤ በሙስሊም አመለካከት እውነቱ አንድ ብቻ ስለሆነ ሃይማኖቶች ሁሉ አንድ ናቸው" ብሏል፣

ውሸት ነው፣ ያልተማረውን ህዝብ ለማዘናጋት ነው፤ አንዱ ከሌላው ጋር የማይገናኝና በፍልስፍና የማይጣጣሙ ሶስት አይነት እምነቶች በአለም ላይ አሉ፤ እነዚህም የአይሁድ ሃይማኖት የክርስቲያን ሃይማኖትና የእስላም ሃይማኖት ናቸው፤ በተለይ የእስልምና ሃይማኖት ከክርስትና ሃይማኖት ጋር በግናቸውም መልኩ ሊገናኝና ሊቀራረብ የማይችል በመካከላቸው የሰማይና የምድር ያህል ርቀት ያለው መሆኑን በክርስቲያኑ ህብረተሰብ ዘንድ በግልጥ መታወቅ አለበት።

ለሙስሊሙ ህብረተሰብ አፈቀላጤዎች የማቀርበው ሌላው ጥያቄ ከ600 ዓመተምህረት በኋላ ራሳችሁን ከክርስትናው አለም አግልላችሁ ለአዋቀራችሁት ሃይማኖት በአጭር ታጥቃችሁ እየተከራከራችሁ እንደገና ሙስሊሙ እስልምናን የራሴነው ብሎ አያወራም ማለታችሁ ማንን ለማታለል ነው? ራሳችሁን ነው? ወይስ ሌላውን ህብረተሰብ የምታታልሉት? ራሳችሁን ከምታታልሉት በስተቀር በአሁኑ ጊዜ የሚታለል ሰብአዊ ፍጡር አለ ብላችሁ አትጠራጠሩ፤ ከዚህ ይልቅ እንደገና እራሳችሁንና የተከተላችሁትን የሀይማኖት ፍልስፍና በጥሞና (በጥንቃቄ) እንድትመረምሩትና እንድታጤኑት እጅግ በጣም ርህሩህ በሆነው በእግዚአብሄር ስም እንለምናችኋለን፣ እንማጠናችኋለን።

## ከሥላሴ አንዱ ለምን ሰው ሆነ?

የመጀመሪያዎቹ ሰዎች አዳምና ሔዋን መሆናቸውን የማያውቅ የለም፤ እግዚአብሔር አዳምና ሔዋንን ፈጥሮ መረን አልሰደዳቸውም፣ በገነት ቦታቸውን ወስኖ የሚበሉትንና የሚጠጡትን አዘጋጅቶ የሚጠብቁትን ሕገና ስርአት ሰጥቶ የፈጠራቸውን አምላክ የሚያመሰግኑበት (የሚፀልዩበት) ሰዓት ለይቶ አስቀመጣቸው፤

በገነት ውስጥ ሶስት እንጨቶች ነበሩ፣ አንዱ፡ ምግባቸወ



ነው፣ ሁለተኛው አትብሉ የተባሉት ዕፀ በለስ ነው፣ ሶስተኛው ዕፀ ህይወት ይባላል፤ ከነዚህ ከሶስቱ አንዲቱ ዕፀ በለስ የፍጡርና የፈጣሪ የገዢና የተገዢ ምልክት (አታድርግ የምትል ህግ) ነበረች። አዳምና ሔዋን በዕፀ በለስ አማካይነት የተሰጣቸውን ህግ ጠብቀው ለሰባት ዓመት ያህል በገነት ተቀመጡ (ኖሩ) ከሰባት ዓመት በኃላ ግን በሰይጣን ተታለው በእፀ በለስ የተሰጣቸውን ህግ ተላልፈው እፀ በለስን በሉ፣ ከፈጣሪያቸው ተጣሉ፣ ከገነት ወጡ ክብራቸውን አጡ። በዚህ ምክንያት የመረረ ለቅሶ አለቀሱ፣ ይሁን እንጂ አዝነው አልቅሰው ይቅርታ ሊያገኙ አልቻሉም ። ታድያ አዳምና ሔዋን እንዴት ይቅርታ ሊያገኙ ቻሉ? ይህ ጥያቄ ነው በሙስሊሙ ህብረተሰብ ሙሀራን ዘንድ ተገቢ ትኩረት ያልተሰጠውና እስከ ዛሬ መልስ ሊያገኝ ያልቻለው ሚስጥር።

ከሥላሴ አንዱ የአብ ቃል ኢየሱስ ክርስቶስ ለምን ሰው ሆነ? የሚል ጥያቄ መነሳት አለበት፣ ከሥላሴ አንዱ ወልድ (ክርስቶስ) ሰው የሆነበት ምክንያት አዳምና ሔዋን ከላይ እንደተገለጠው እፀ በለስን በልተው ከፈጣሪያቸው በመጣላታቸው ምክንያት አዝነው አልቅሰው ይቅርታ በጠየቁ ጊዜ ፍጠረን ሳይሉት የፈጠራቸው አምላክ ለቅሶአቸውን ሰምቶ አዘናቸውን ተመልክቶ "በአምስት ቀን ተኩል መጥቼ አድንሀለሁ" የሚል ተስፋ ሰጠው፣ አምስት ቀን ተኩል ማለት አምስት ሺህአምስት መቶ ዘመን ማለት ነው፤ አምስት ሺህ አምስት መቶ ዘመን ሲፈፀም ከልጅ ልጅህ ተወልጄ በመስቀል ላይ ሞቼ ተነስቼ አድንሀለሁ ሲለው ነው፤ ተናገር የማያስቀር የሰጠውን ተስፋ የማያጥፍ አምላክ ከመወለዱ በፊት ይወርዳል ይወለዳል በማለት የመወለዱን ዜና (ትንቢት) በነብያት ተናገሯል፤ ትንቢት ከተናገሩት ነቢያት አንዱ ኢሳያስ "ድንግል በድንግልና ትፀንሳለች፣ ወንድ ልጅ ትወልዳለች፣ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች" ሲል ትንቢት ተናገሯል፣ ነቢዩ ዳንኤልም "እስከ መሢህ (ክርስቶስ) ድረስ ቤተመቅደስ (ኢየሩሳሌም) ትሠራለች" ሲል ትንቢት ተናገርአል፣ ቅዱስ ገብርኤልም፣ እነሆ ትፀንሻለሽ ወንድም ልጅ ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ በለሽ ትጠሪያለሽ፣ የልዑል ልጅም ይባላል፣



www.ethiopianorthodox.org

የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፣ በያቆብም ቤት ለዘላለም ይነግሳል፣ ለመንግስቱም ፍፃሜ የለውም" ሲል ለድንግል ማርያም አብስሯታል፣ ኢሳ.7 ቁ.14፣ዳን.9ቁ25፣ ሉቃ.1 ቁ.28።

"አስቀድሞ ቃል ነበር፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበር፣ቃልም እግዚአብሔር ነበር፣ ሁሉ በእርሱ ሆነ፣ ያለእርሱ ምንም የሆነ (የተፈጠረ) የለም፤... ቃልም ሥጋ ሆነ፣ በእኛ ላይም አደረ" ዮሐ.1 ቁ.14፣ 1ጢሞ.3 ቁ.16፣

ቁርዓንም "ማርያም ሆይ! አላህ ከእርሱ በሆነው ቃል ስሙ አልመሲህ፣ ኢሳ የማርያም ልጅ በዚህ አለምና በመጨረሻው አለም የተከበረ፣ ከባለሟሎቹ በሆነ ልጅ ያበስርሻል" ይላል፣ ቁርዓን 3 ቁ.45።

ክርስቶስ አምላክ ወልደ አምላክ ለመሆኑ በዮሐንስ እጅ በተጠመቀ ጊዜ "እነሆ ሰማዮች ተከፈቱ፣ መንፈስ ቅዱስ በእርግብ አምሳል ወርዶ በራሱ ላይ ተቀመጠ፣ ከሰማይም ድምፅ መጣ ፣ እንዲህ ሲል የምወደው ደስታዬን የምገልጥበት ልጄ ይህ ነው" ማቴ.3 ቁ.16 ማቴ.17 ቁ.5-6፣

"አብ በማንም አይፈርድም፣ ነገር ግን ፍርዱን ሁሉ ለልጁ ሰጠው" ፤ ዮሐ.5 ቁ.22 ፤

"እኔና አብ አንድ ነን"፤ ዮሐ.10 ቁ.30፤

"እኔን ያየ አብን አየ" ፤ ዮሐ.14 ቁ 9፤

"እግዚአብሔር እንዲሁ አለሙን ወዷልና አንድ ልጁን እስቲለውጥ ድረስ በእርሱ ያመነ ሁሉ እንዳይጠፋ የዘላለም ህይወት ትሆንለት ዘንድ እንጂ፣ እግዚአብሄር ልጁን ወደ አለም አላከውምና ዓለምን ሊኮንን፣ ነገር ግን አለም ይድንበት ዘንድ ነው፤ በርሱ ያመነ አይኮነንም፣ የማያምንበት ግን አሁን የተኮነነ ነው፣ በአንድ በእግዚአብሔር ልጅ ስም አላመነምና" ዩሐ.3 ቁ.16-18፤

"በዚህ የእግዚአብሔር ፍቅር ተገለጠ እግዚአብሔር አንድ ልጁን ወደኛ ወደአለም ልኳልና በእርሱ እንድንበት ዘንድ" 1ኛዩሐ.4 ቁ.9፤

እንግዲህ አባትና ልጅ (አብና ወልድ) አደባባይ ወጥተው እጅ ለእጅ ተያይዘው አባት ልጄ ነው ልጅም አባቴ ነው በማለት ተማምነው መስክረውና አረጋግጠው የሰጡትን



www.ethiopianorthodox.org

መተማመኛ ከጎረቤት አንዱ ተነስቶ አንተ አባቱ አይደለህም አንተም ልጁ አይደለህም በማለት ለማስተባበል ቢሞክር ምን ትሉታላችሁ? "ከባለቤቱ ያወቀ ቡዳ ነው" ትሉታላችሁ እንጂ ሌላ ምን ትሉታላችሁ? የሙስሊሙ ህብረተሰብ አፈቀላጤዎችም እንደዚሁ ናቸው፣ አብ ይህ ልጄ ነው ወልድም አባቴነው እያሉ በአደባባይ በህዝብ ፊት አባትና ልጅ ልጅነታቸውን አረጋግጠው እየተናገሩ አፈ ቀላጤዎች ግን "አላህ አንድ ነው አይወልድም አይወለድም" በማለት ዓይናቸውን አፍጥጠው ጆሯቸውን ሸምጥጠው መሟገታቸው ምን ይባላል? ሙግቱስ ከማን ጋር ነው? ከእግዚአብሔር ጋር አይደለምን? መሐሪው አምላክ እየሱስ ክርስቶስ ይቅር ይበላችሁ፤ ሰሚ ጆሮ አስተዋይ አይምሮ ይስጣችሁ፤ አሜን።

## የክርስቲያኖች መለኮታዊ መመሪያ

በአዲስ ኪዳን ከኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠን ክርስቲያናዊ መመሪያ "ስላሴ በስም በአካል ሶስት ናቸው" ማለት ስማቸው "እግዚአብሔር አብ እግዚአብሔር ወልድ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ" ይባላል፤ የአብ አካል አለው፣ የወልድ አካል አለው፣ የመንፈስ ቅዱስ አካል አለው፣ በመለኮትና በባህርይ ግን "አንድ እግዚአብሔር" ይባላሉ፤

በስላሴ ስም "ያመነ የተጠመቀ ይዳን፣ ያላማነ ያልተጠመቀ ግን ይኮነን" ፤ማር.16 ቁ.16፤

"ከውሀና ከመንፈስ ካልተወለደ (ካልተጠመቀ) ወደ እግዚአብሔር መንግስት ይገባ ዘንድ አይችልም"፤ ዩሐ.5 ቁ.7፤

"በሰማይ የሚማሰክሩ ሶስተ ናቸው፣ እነርሲም አብ ቃልና መንፈስ ቅዱስ እሊህ ሶስቱ አንድ ናቸው"፤ 1ዩሐ.5 ቁ.7፤

"እንግዲህ ሂዱና አህዛብን ሁሉ አስተምሩ፤ በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ስም አጥምቋቸው" ይላል፤ ማቴ.28 ቁ.19።

"ወስብሐት ለእግዚአብሐር"
አነሳስቶ ላስጀመረኝ
አስጀምሮ ላስፈፀመኝ
እግዚአብሔርክብር ምስጋና ይገባዋል አሜን ።